የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሰላሳ አንደኛ ዓመት ቁጥር ፶፯
አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

31st Year No. 57
ADDIS ABABA 28TH July, 2025

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፮/፪ሺ፲፯

የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አዋጅ ………………………………………………………ገጽ ፲፰ሺ፱፻፶፯

## Content

Proclamation No. 1386/2025

Ethiopian Disaster Risk Management Proclamation………….....................Page 18957

### አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፮/፪ሺ፲፯

### የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አዋጅ

መንግስት ማንኛውም የተፈጥሮ እና ሰው ሰራሽ አደጋ በዜጎች ላይ እንዳይደርስ የመከላከልና አደጋው ሲደርስም ለተጎጂዎች የሰብዓዊ ድጋፍ በጊዜ እንዲደርስ የማድረግ ሕገ-መንግስታዊ ኃላፊነት ያለበት በመሆኑ፤

አደጋን በመከላከል፣ በማቅለል፣ ዝግጁነትን በማረጋገጥ፣ ወቅታዊ ምላሽ በመስጠትና በተሻለ ሁኔታ መልሶ በማቋቋም ረገድ የፌደራልና የክልል የአስተዳደር ተቋማትን የውስጥ አቅም መገንባት አስፈላጊ በመሆኑ፤

ቅጽበታዊ አደጋ ሲከሰትና ከአቅም በላይ ሲሆንም የአስቸኳይ ጊዜ እወጃ ሥርዓት በመዘርጋትና ተግባራዊ በማድረግ ከታችኛው እስከ ፌደራል መዋቅር በተቀመጠው የአደጋ ስጋት ገደብ መሠረት የድጋፍ አሰጣጥ ሥርዓቱን ተግባራዊ የማድረግን አስፈላጊነት በማጤን፤

የኢትዮጵያ አደጋ ሥጋት ሥራ አመራር የቅድመ-አደጋ ፣ የአደጋ ወቅትና የድህረ-አደጋ ተግባራትን ውጤታማ ለማድረግ የሰብዓዊ ድጋፍ፣ የዘላቂ ልማት እና የሰላም ግንባታ ዕቅዶችን ማስተሳሰር አስፈላጊ በመሆኑ፤

### PROCLAMATION NO 1386 /2025

### ETHIOPIAN DISASTER RISK MANAGEMENT PROCLAMATION

**WHEREAS,** the Government has a Constitutional obligation to take measures to prevent any natural and man-made catastrophes, and to provide instantaneous assistance for victims in the event of disasters;

**WHEREAS,** it is essential to build the internal capacity of Federal and Regional institutions in areas of disaster prevention, preparedness, mitigation, timely response and improved rehabilitation and reconstruction;

**CONSIDERING,** the necessity of establishing and implementing an emergency declaration system in situations where there is an emergency disaster that is beyond capacity, as well as implementing the support provision system in accordance with the threshold that has been established from bottom to federal structure;

**WHEREAS,** it is found vital for integrating the pre-disaster, during disaster, and post-disaster activities of Ethiopian Disaster Risk Management with humanitarian assistance, sustainable development, and peace-building initiatives;

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፫፻፹፮/፪ሺ፲፯" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል::

### ፪. ትርጉም

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ **"አደጋ"** ማለት መንስዔው የተፈጥሮ ወይም ሰው ሰራሽ ሆኖ የሕብረተሰቡን የዕለት ከዕለት ኑሮ በከፍተኛ ሁኔታ የሚያስተጓጉል፤ በሰው፣ በንብረት፣ በኢኮኖሚ ወይም በአካባቢ ላይ መጠነ ሰፊ ጉዳትና ተፅዕኖ የሚያስከትልና በአደጋው የተጠቃው ሕዝብ የራሱን አቅምና ጥሪት ተጠቅሞ ለመቋቋም ከአቅሙ በላይ የሆነ ክስተት ነው፤

፪/ **"የአደጋ ስጋት"** ማለት በሥርዓት፣ በማኅበረሰብ ወይም በሕብረተሰብ ውስጥ በተወሰነ የጊዜ ሂደት ሊከሰት ይችላል ተብሎ የሚገመትና በተለያዩ ሁኔታዎች መስተጋብር የሚወሰን ሲሆን እነዚህም የአደጋ ክስተት መንስዔ፣ ተጋላጩ አካል ለአደጋው ያለው ቅርበት፣ ተጋላጭነትና የመቋቋም አቅም ናቸው፤

፫/ **"የአደጋ ሥጋት ግምገማ"** ማለት አደጋ ሊያስከትሉ የሚችሉ ሁኔታዎችን መለየት፤ የአደጋ መሠረታዊ ጠባያት ማለትም አደጋ ሊከሰትበት የሚችልበት ቦታ፣ የአደጋውን ጥንካሬ፣ ድግግሞሽንና የመከሰት ዕድልን መመርመር እንዲሁም የአካላዊ፣ የማኅበራዊ፣ የጤና፣ የአካባቢያዊና የኢኮኖሚያዊ ተጋላጭነት ትንታኔ እና ሊከሰት ከሚችለው አደጋ ሁኔታ ጋር በጥቅም ላይ ያሉ የተሻሉና አማራጭ የመቋቋሚያ አቅሞች ውጤታማነት ግምገማ ነው፤

**NOW,THEREFORE,** in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

## SECTION ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Ethiopian Disaster Risk Management Proclamation No.1386/2025".

### 2. Definitions

In this Proclamation, unless the context requires otherwise:

1/ **"Disaster"** means a significant disruption to society's daily life caused by natural or man-made disasters, resulting in widespread human, material, economic, or environmental losses that exceed the affected people's ability to cope with their own resources;

2/ **"Disaster Risk"** means the potential loss of life, injury, or destroyed or damaged assets that could occur in a system, society, or community over a specific period of time, as determined probabilistically as a function of hazard, proximity of the vulnerable body to the disaster, vulnerability, and resilience capacity;

3/ **"Disaster Risk Assessment"** means the identification of hazards, a review of their technical characteristics such as location, intensity, frequency, and probability, as well as an analysis of vulnerability, including physical, social, health, environmental, and economic dimensions, and an evaluation of the effectiveness of current and alternative coping capacities in relation to likely risk scenarios;

፬/ **"የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር"** ማለት የአደጋ አምጪ ስጋቶችና ክስተቶች ሊያስከትሉዋቸው የሚችሉ አሉታዊ ተፅዕኖዎችን ለመቀነስ በሥራ ላይ የሚውሉ ፖሊሲዎችና ስልቶች፣ የመቋቋሚያ አቅሞች የሚተገበርባቸው አስተዳደራዊና የሕግ ማዕቀፎች፣ ተቋማት፣ የአሰራር ሥርዓትና አቅሞችን የመጠቀም ሂደት ነው፤

፭/ **"የአደጋ ሥጋት ቅነሳ"** ማለት መሠረታዊ የአደጋ መንስዔዎችን በመተንተንና በመምራት፣ የሕብረተሰብንና የንብረትን የአደጋ ተጋላጭነትን በመቀነስ ፣ መሬትና አካባቢን በአግባቡ በማስተዳደርና አሉታዊ ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ክስተቶችን በመቀነስ እና የዝግጁነት አቅም በማጠናከር፤ የአደጋ መነሻ ምክንያቶች ላይ ጥናቶችን በማድረግ የአደጋ ክስተት ሥጋትን የመቀነስ ተግባር ነው፤

፮/ **"ቅድመ-ማስጠንቀቂያ ሥርዓት"** ማለት በአደጋ መንሥዔ እና በተያያዥ አደጋዎች ሊጠቁ የሚችሉ ግለሰቦች፣ የማኅበረሰብ ክፍሎችና ተቋማት እንዲዘጋጁ የማድረግና ተገቢውን እርምጃ በወቅቱ ለመውሰድና ሊደርስ የሚችለውን ጥፋትና ጉዳት ለመቀነስ እንዲያስችል መረጃን ለማሰባሰብ፣ ለመተንተን፣ ለመተንበይ፣ እና አስቀድሞ ለማስተላለፍና ለማሰራጨት የሚያስችል የተደራጀ አቅም ነው፤

፯/ **"አደጋ አምጪ ክስተት"** ማለት የሕይወት መጥፋት፣ የአካል ጉዳት ወይም ሌላ የጤና ተፅዕኖ፤ የንብረት ጉዳት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ መስተጓጎል ወይም የአካባቢ መራቆት ሊያስከትል የሚችል ሂደት ነው፤

፰/ የእሳት ኮድ" ማለት የእሳት አደጋን ለመከላከል እና ለመቀነስ የሚያገለግሉ በሚመለከተው ባለሥልጣን የተደነገጉት ደንቦች ወይም መስፈርቶች ነው፤

፱/ **"ማቅለል"** ማለት ያለን ወይም ሊከሰት የሚችልን አደጋ አምጪ ክስተትን አሉታዊ ተፅዕኖን መቀነስ፣ መወሰን ወይም ማሳነስ ሲሆን መዋቅራዊ ወይም መዋቅራዊ ያልሆኑ እርምጃዎችን ይጨምራል፤

4/ **"Disaster Risk Management"** means the systematic process of using Administrative and Legal frameworks, institutions, and operational capabilities to implement plans, policies, and better coping capacities in order to mitigate the adverse impacts of hazards;

5/ **"Disaster Risk Reduction"** means the practice of reducing disaster risk vulnerability by conducting studies on the root causes of disaster, reducing exposure to disaster, reducing disaster vulnerability of people and property, wise land and environmental management, and strengthening improved preparedness for adverse events;

6/ **"Early Warning System"** means a set of organized capacities needed to generate and disseminate timely and meaningful warning information to enable individuals, communities and organizations threatened by a hazard to prepare and to act appropriately and in sufficient time to reduce the possibility of harm or loss;

7/ **"Hazard''** means a potentially harmful physical event, phenomena, or human behavior that may result in the loss of life or injury, property damage, social and economic disruption, or environmental degradation;

8/ "Fire Code" means the rules or requirements established by the relevant authority to prevent and reduce fire hazards;

9/ **"Mitigation''** means actions or processes that lessen or limit the adverse impacts of hazards, whether active or anticipated, and includes structural or non-structural interventions;

፲/ **"ዝግጁነት"** ማለት በቅድመ አደጋ፣ በአደጋ ወቅት እና በድህረ አደጋ ሊከሰት ከሚችል ወይም አይቀሬ ከሆነ የአደጋ ተፅዕኖ ውጤታማ በሆነ መልኩ ለመገመት፣ ለመመለስ እና መልሶ ለማቋቋም የአደጋ ሥጋት ስራ አመራር ኃላፊነት ባለባቸው የመንግሥት ተቋማት፤የግል ተቋማትና የህብረተሰብ ክፍሎች የተገነባ ዕውቀትና አቅም ነው፤

፲፩/ **"የአደጋ ስጋት መግለጫ"** ማለት የአደጋ መጠንና ባህሪ ለመወሰን በመደበኛ ሥጋት ግምገማ፣ የአደጋ ተጋላጭነት፣ የአየር ንብረት ለውጥና የመቋቋም አቅም ላይ የተደረገ ትንተና እና አመላካች የዳሰሳ ጥናት ውጤት ነው፤

፲፪/ **"አደጋ መከላከል"** ማለት ነበርና አዲስ የሆኑ የአደጋ ሥጋቶችን ለማስወገድ የሚወሰድ ድርጊትና እርምጃ ሲሆን ይህም አደጋን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ በማይቻልበት ሁኔታ ተጋላጭነት መቀነስን ይጨምራል፤

፲፫/ **"ማገገም"** ማለት በአደጋ የተጎዱ ሰዎች ወይም የማኅበረሰብ ኢኮኖሚያዊ፣ አካላዊ፣ ማኅበራዊ፣ ባሕላዊና አካባቢያዊ ሀብቶች፣ አገልግሎቶችና ሥርዓቶች እንዲሁም እንቅስቃሴዎች ላይ የተፈጠሩ ጉዳቶችን በዘላቂነት በመፍታት ለወደፊቱም የሚመጣን አደጋ ሥጋትን ለማስወገድና ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የመመለስ ወይም የማሻሻል ሂደት ነው፤

፲፬/ **"መልሶ ማቋቋም"** ማለት አደጋ ከተከሰተ በኋላ በአደጋው የተጎዱ ሰዎችና የህብረተሰብ ክፍሎችን ወደ መደበኛ እንቅስቃሴ ለመመለስ እንዲሁም ጉዳት በደረሰበት አካባቢ፣ ማኅበረሰብ እና የኢኮኖሚ ዘርፍ ላይ ወደፊት ሊከሰት የሚችልን አደጋ ለመቋቋም የሚወሰድ እርምጃና ሂደት ነው፤

፲፭/ **"ምላሽ"** ማለት ሕይወትን ለማዳን፣ የኑሮ መሠረቶች ላይ የሚደርስ ተፅዕኖን ለመቀነስ፣ የሕዝብ ደህንነትን ለማረጋገጥ እና አደጋ የደረሰባቸውን የሕብረተሰብ ክፍሎች መሠረታዊ የሕልውና ፍላጎቶችን ለማሟላት አደጋ ከመከሰቱ በፊት፣ በአደጋ ወቅትና ከአደጋ በኋላ በቀጥታ የሚወሰድ እርምጃ ነው፤

10/ **"Preparedness''** means knowledge and capacities developed by relevant government agencies and sections of society responsible for disaster risk management to successfully anticipate, respond to, and recover from the impacts of likely, imminent, or existing disasters;

11/ **"Disaster Risk Profile''** means an analysis and indicative survey outcome of a regular risk assessment conducted to determine the nature and extent of risk by analyzing disaster vulnerabilities, climate change and resilience capacities;

12/ **"Risk Prevention''** means activities and measures taken to avoid existing and emerging disaster risks, which may also include reducing vulnerability in situations where complete avoidance is unattainable;

13/ **"Recovery''** means the process of restoring or improving economic, physical, social, cultural, and environmental assets, systems, and activities of disaster-affected persons or society in order to avoid and reduce future disaster risk;

14/ **"Rehabilitation''** means measures taken after a disaster to restore the regular functioning of impacted persons and communities, as well as to build resilience for future shocks;

15/ **"Response''** means actions taken directly before, during and immediately after a disaster in order to save lives, mitigate impacts on livelihoods, ensure public safety and meet the basic subsistence needs of the people affected;

፲፮/ **“የመቋቋም ችሎታ”** ማለት ለአደጋ ስጋት የተጋለጠ ሥርዓት፣ ዜጋና ማህበረሰብ የመቋቋም፣ የመቀበል፣ የማስተናገድ፣ የመላመድ፣ የመለወጥ እና ከአደጋው ተፅዕኖ በጊዜው እና ውጤታማ በሆነ መልኩ የማገገም እንዲሁም በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ሥርዓት ያሉትን መዋቅሮችና እንቅስቃሴዎች ጠብቆ የማቆየትና ወደነበሩበት ሁኔታ መመለስን ይጨምራል፤

፲፯/ **“ተጋላጭነት”** ማለት በአካላዊ፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊ እና አካባቢያዊ ሁኔታዎች ወይም ሂደቶች የሚወሰን ሆኖ ግለሰብን፣ ማህበረሰብን እና ተጋላጭ የሕብረተሰብ ክፍሎችን ለአደጋ አምጪ ክስተት ተፅዕኖ መጋለጥን የሚያባብስ ሁኔታ ነው፤

፲፰/ **“የአደጋ ስጋት ገደብ”** ማለት አደጋው በደረሰበት አካባቢ የሚገኝ የአመራር ሥርዓት፤ ሀብት እና አቅም መሠረት ያደረገ ሊከሰት ከሚችለው ወይም በተከሰተ አደጋ የጉዳት መጠን በየደረጃው ለመከላከል፤ ለማቅለል፣ ለመዘጋጀት፤ ምላሽ ለመስጠት፤ መልሶ ለማቋቋም ከታችኛው የአስተዳደር እስከ ፌደራል እርከን በራስ አቅም ጉዳት የደረሰበትን ሕብረተሰብ ክፍል ድጋፍ ለመስጠት ለመወሰን የሚያገለግል ሥርዓት ነው

፲፱/ **“የአደጋ እወጃ”** ማለት አደጋው በደረሰበት አካባቢ የሚገኝና ጉዳዩ የሚመለከተው አካል በአደጋ ስጋት ገደብ መሠረት የአደጋው መጠንና ተፅዕኖ ባለው አቅም በአጥጋቢ ሁኔታ ለመቋቋም የማይቻል መሆኑን በይፋ በመግለፅ በሰው ሕይወትና በኑሮ መሠረቶች ላይ የከፋ ጉዳት እንዳይደርስ የድረሱልኝ ጥሪ የሚጠይቅበት ሥርዓት ነው፤

፳/ **“የአደጋ ተጎጂ”** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ጉዳት የደረሰበት ሰው ነው፤

፳፩/ **“ስትራቴጅክ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት”** ማለት በየአስተዳደር እርከኑ ለመጠባበቂያነት የሚያዝና የሚተዳደር ወይም በአደጋ ጊዜ የሚገጥምን የምግብ እጥረት ለመቋቋምና የዕለት ደራሽ ሰብዓዊ ድጋፍ በብድር ለማቅረብ የሚያዝ እንደ እህል፣ ዘይት፣ አልሚ ምግብ፣ ጥራጥሬና የመሳሰሉትን የሚያካትት ነው፤

16/ **“Resilience’’** means the ability of a system, citizen, or society to resist, absorb, accommodate, adapt to, transform, and recover from the effects of a hazard in a timely and efficient manner, including the preservation and restoration of its essential basic structures and functions through risk management;

17/ **“Vulnerability’’** means the conditions created by physical, social, economic, and environmental elements or processes that make an individual, community, assets, or systems more prone to the impacts of hazards;

18/ **“Disaster Risk Threshold”** administrative system, resource and capacity available from the bottom to federal administrative levels found at the place where the disaster occurred to protect, mitigate, prepare, respond, and rehabilitate the disaster-affected segment of the society based on own capacity;

19/ **“Declaration of Disaster”** means a system in which an official announcement for a support will be made by the responsible authority in the disaster affected area to protect sever damage on human lives and livelihoods due to the occurrence of a disaster which is in accordance with the disaster risk threshold beyond its capacity in its scale or impact to effectively address;

20/ **“Affected People’’** means those people who are directly or indirectly impacted by a natural or man-made disaster;

21/ **“Strategic Food Reserve”** includes a strategic food stockpile stored and administered at each administrative level to address food shortages during disasters and to provide emergency humanitarian assistance through loan items such as crops, oil, food, cereals, and related items;

፳፪/ **"ስትራቴጂክ የመጠባበቂያ ምግብ-ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ ክምችት"** ማለት በየአስተዳደር እርከኑ ለመጠባበቂያነት የሚያዝና የሚተዳደር ወይም በአደጋ ጊዜ የሚገጥም አስቸኳይ የግልና የጋራ ፍላጎትን በብድር ለማሟላት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን የሚያጠቃልል ነው፤

፳፫/ **"ቅጽበታዊ አደጋ"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ የአደጋ መንስዔ ምክንያቶች ባልተገመተ ሁኔታና መጠን የሚፈጠር ክስተት ሆኖ በሰው ሕይወት፣ በተፈጥሮ ሀብት፣ ንብረት፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳትን የሚያስከትል ሲሆን እንደ የቤትና ሰደድ እሳት፤ ጎርፍ፤የመሬት መንሸራተትና መሰንጠቅ፤ ርዕደ መሬት፣ አውሎ ንፋስ፤ ወረርሽኝ የመሣሠሉትን ያጠቃልላል፤

፳፬/ **"የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ"** ማለት በዚህ አዋጅ ከተዘረዘሩት የገቢ ምንጮች የሚሰበሰብ ለአደጋ ስጋት ምላሽ ለመስጠት እንዲያስችል የሚሰበሰብ የገንዘብ ሀብት ነው፤

፳፭/ **"የምግብ ዋስትና እጥረት"** ማለት በተፈጥሮ ወይም በሰው ሰራሽ አደጋዎች ምክንያት በአቅርቦት፤ በተደራሽነት፤ በአጠቃቀምና በመግዛት አቅም ውስንነት ምክንያት ዕለታዊ የምግብና ሥነ-ምግብ ፍላጎትን ማሟላት ያለመቻል ሁኔታ ነው፤

፳፮/ **"ሰብዓዊ ድጋፍ"** ማለት በሰው ሕይወትና በኑሮ መሠረቶች ላይ አደጋ ለአጋጠማቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ማንኛውንም ዓይነት ገደብ ሳይጣል በሰብዓዊነት፤ በገለልተኝነት፤ በግልፀኝነት፤ በፍትሃዊነት፤ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ በዓይነት፤ በገንዘብ ወይም በሁለቱም ዓይነት የሚሰጥ የድጋፍ ዓይነት ነው፤

፳፯/ **"የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ"** ማለት በአደጋ ጊዜ የተጎጂውን ህዝብ ሕይወት ለማዳን፣ የኑሮ መሠረትን ለመታደግና በጊዜያዊነት ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶችና አገልግሎቶች ማቅረብና ማከፋፈል ነው፤

፳፰/ **"በጎ ፍቃደኞች"** ማለት ከህብረተሰቡ፣ ከተለያዩ መንግስታዊና መንግስታዊ ካልሆኑ፣ የግል ተቋማት፣ የተውጣጡ በተፈጥሮ እና በሰው ሰራሽ አደጋዎች ላይ በፍቃደኝነትና በነፃ አገልግሎት ለመስጠት ሙያዊ ስልጠና የወሰዱ፣ መልካም ሥነ-ምግባር ያላቸው ሰዎች ናቸው፤

22/ **"Strategic non-food materials reserve"** includes materials stockpile stored and administered at each administrative level to address in loan the immediate private and common needs during disaster;

23/ **"Rapid-onset disasters"** means unanticipated disaster phenomenon caused by natural or manmade factors and result in loss of lives and damage to assets, socio-economics and the environment including earthquake, land slide, structural and wild fire, flush flood, tornedo, epidemic, etc;

24/ **"Ethiopian Disaster Risk Response Fund"** means a financial resource reserved to respond to a disaster and collected from sources listed in this Proclamation;

25/ **"Shortage of food supply"** means is a situation of inability to fulfill daily food and gastronomic needs due to natural or manmade disaster affecting the supply, accessibility, utilization and purchasing capacity;

26/ **"Humanitarian Assistance "** means a type of support provided in-kind, cash, or both to a section of society whose livelihood and human life are affected by disaster, without imposing any limitations, but based on humanity, impartiality, transparency, fairness, and without any preconditions;

27/ **"Emergency Response"** means supply and distribution of food and non-food items and services on a temporary basis to save the lives and livelihoods of the affected people during disaster;

28/ **"Volunteers"** means people with and integrity drawn from the society, governmental and non-governmental and private entities and who have received training to provide free services on natural and manmade disaster;

፳፱/ **"መሪ የዘርፍ ተቋማት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳ ሥር የተዘረዘሩት የፌደራል ተቋማት ናቸው፤

፴/ የሰብዓዊ ድጋፍ የምግብ ቁሳቁስ መያዣ የጥራት ደረጃ" ማለት ለእርዳታ የሚቀርብ ማንኛውም ዓይነት ምግብ የጥራት ደረጃውን የጠበቀ ፤ ባዕድ ነገሮች ያልተቀላቀለበት ፤ በመያዣው ላይ የምርቱ ዓይነት፣ የተመረተበት እና የመጠቀሚያ ጊዜ ያለው፣ የምርት መጠን፣ ወ.ዘ.ተ የመሳሰሉትን ዝርዝር መግለጫዎች የያዘ ነው፡፡

፴፩/ **"ክልል"** ማለት በኢፌዲሪ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯ መሠረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፴፪/ **"ኮሚሽን"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ነው፤

፴፫/ **"ምክር ቤት"** ማለት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ መሠረት የተቋቋመው የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ምክር ቤት ነው፤

፴፬/ **"ሰው"** ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፴፭/ ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀው አነጋገር የሴትንም ያካትታል፡፡

## ፫. <u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>

ይህ አዋጅ በመላ ሀገሪቱ በሚከናወኑ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ተግባራት ላይ ሁሉ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ፬. <u>የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መሠረታዊ መርሆዎች</u>

የሚከተሉት የኢትዮጵያ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መሠረታዊ መርሆዎች ናቸው:-

፩/ ሰብዓዊነት፤

፪/ ገለልተኝነት፤

፫/ ግልፀኝነት፤

፬/ አለማዳላት፤

፭/ አሳታፊነት፤

፮/ ትብብር፤

29/ **"Lead Sector Institutions"** means Federal institutions listed under Article 20 of this Proclamation;

30/ "Quality standard for humanitarian food aid packaging" means that any type of food provided for aid meets quality standards; is free from foreign substances; and has detailed information on the packaging, such as the type of product, date of manufacture and expiry date, quantity of product, etc.

31/ **"Region"** means any State established in accordance with Article 47 of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, including the city Administration of Addis Ababa and Dire Dawa;

32/ **"Commission"** means the Ethiopian Disaster Risk Management Commission established by Article 5 of this Proclamation;

33/ **"Council"** means the Ethiopian Disaster Risk Management Council established by Article 12 of this Proclamation;

34/ **"Person"** means any natural or juridical person;

35/ Any expression in the masculine gender shall also apply to the feminine gender.

## 3. <u>Scope of application</u>

This Proclamation shall be applicable against all disaster risk management activities carried throughout the country.

## 4. <u>Basic Principles of Disaster Risk Management</u>

The followings are the basic principles of Ethiopian Disaster Risk Management:

1/ Humanity;

2/ Impartiality;

3/ Transparency;

4/ Non-discrimination;

5/ Participatory;

6/ Collaboration;

፯/ አካታችነት፣

፰/ ተጠያቂነት፣

## ክፍል ሁለት

## የኢትዮጵያ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን እና ምክር ቤት

### ፭. የኮሚሽን መቋቋም

፩/ ኮሚሽኑ ራሱን የቻለ የፌደራል መንግሥት አስፈጻሚ አካል ሆኖ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ ተጠሪነት ለጠቅላይ ሚኒስትሩ ይሆናል፡፡

### ፮. የኮሚሽኑ አደረጃጀት

ኮሚሽኑ፡-

፩/ ምክር ቤት፣

፪/ በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሾም ኮሚሽነር እና እንደ አስፈላጊነቱ ምክትል ኮሚሽነሮች፣ እና

፫/ አስፈላጊ ሰራተኞች፣ ይኖሩታል፡፡

### ፯. የኮሚሽኑ ዓላማዎች

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ውጤታማ አደጋ መከላከልን፣ ማቅለልን፣ ዝግጁነትን፣ ምላሽን፣ መልሶ ማቋቋምን እና የማህበረሰብን የመቋቋም ብቃት መገንባትን የሚጨምር ሁለንተናዊ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት መዘርጋት፣

፪/ በፌደራል እና በክልል ያሉ አቅሞችን በማጠናከር ሁሉን አቀፍ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት በመዘርጋትና የተቀናጀ ዕቅድና ትብብርን በማስፋፋት በዘላቂ ልማት ፕሮግራሞችና ፕሮጀክቶች በሚመለከታቸው መሪ የዘርፍ ተቋማት ውስጥ ተግባራዊ እንዲደረግ በማድረግ የአደጋ ስጋትንና በአደጋ ምክንያት ሊከሰት የሚችልን ጉዳት መከላከልና መቀነስ፣

፫/ የተናበበ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃዎች ትንተናና የትንበያ ሥርዓት በመዘርጋት በሰው ሕይወት፣ በኑሮ መሠረት፣ በመሰረተ-ልማት ላይ የሚደርሱ ጉዳቶችን ለመቀነስና መከላከል የሚችል ሥርዓት መኖሩን ማረጋገጥ፣

7/ Inclusivity;

8/ Accountability.

## SECTION TWO

## ETHIOPIAN DISASTER RISK MANAGEMENT COMMISSION AND COUNCIL

### 5. Establishment of the Commission

1/ The Commission is hereby established as an autonomous Federal Government Executive body.

2/ The Commission shall be accountable to the Prime Minister.

### 6. Organization of the Commission

The Commission shall have:

1/ The Council;

2/ A Commissioner appointed by the Prime Minister, and Deputy Commissioners as may be necessary; and

3/ The necessary staff.

### 7. Objectives of the Commission

The Commission shall have the following objectives:-

1/ Establish comprehensive disaster risk management system for effective disaster prevention, preparedness, mitigation, response, recovery, and building resilience capacity of community;

2/ Prevent and reduce disaster risks and potential damage caused by disasters by strengthening capacities at the Federal and Regional levels, establishing a comprehensive disaster risk management plan, and promoting coordinated planning and collaboration integrating in lead sector institutions' sustainable development programs and projects;

3/ Ensure the existence of a system that can mitigate and prevent damages to human lives, livelihoods and infrastructures through a coordinated early warning information analysis and forecast system;

፬/ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ግንዛቤና ንቃተ ህሊናን በማጎልበት ለአደጋ ስጋት የማይበገር ህብረተሰብ በአገር ደረጃ መገንባት፤

## ፰. ዋና መሥሪያ ቤት

የኮሚሽኑ ዋና መሥሪያ ቤት አዲስ አበባ ሆኖ እንደ አስፈላጊነቱ በሀገሪቱ ሌሎች ሥፍራዎች ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች ሊኖሩት ይችላል፡፡

## ፱. የኮሚሽኑ ተግባር እና ኃላፊነት

ኮሚሽኑ የሚከተሉት ተግባር እና ኃላፊነት አሉት፡-

፩/ የዘርፉን ፖሊሲ፣ ስትራቴጂ፣ የሕግ ማዕቀፍና ስታንዳርዶች ያመነጫል፣ ያዘጋጃል፤ በሚመለከተዉ አካል ሲጸድቅም ስራ ላይ ያውላል፤

፪/ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር እቅድን ከክልሎችና ከመሪ የዘርፍ ተቋማት በመሰብሰብና በማቀናጀት ዓመታዊ ሃገር አቀፍ የአደጋ ሥጋት የቅነሳ እቅድ ያዘጋጃል፤ ለመንግስት ያቀርባል፤ ሲፀድቅም ተግባራዊ ያደርጋል፤

፫/ መሪ የዘርፍ ተቋማት እና የግል ተቋማት የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራትን ከእቅዶቻቸው ጋር አካተው መተግበራቸውን ይከታተላል፤ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ድጋፍ ያደርጋል፤

፬/ ለአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዘርፈ-ብዙ የመረጃ ሥርዓት እና ፕሮፋይል በማደራጀት አገራዊ የቅድመ ማስጠንቀቂያ መረጃ ትንተና እና ትንበያ በማድረግ ምላሽ እንዲሰጥ አግባብነት ካላቸው ተቋማት ጋር በትብብር ይሰራል፤

፭/ ከክልሎች አቅም በላይ ሲሆን ወይም የድጋፍ ጥያቄ ሲቀርብ እና በኮሚሽኑ ተቀባይነት ሲያገኝ ኮሚሽኑ በራሱ ከያዘው መጠባበቂያ ክምችት ወጭ በማድረግና በማጓጓዝ ድጋፍ ያደርጋል፤ እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እና በመንግስት ሲወሰን የሚተካ ከስትራቴጅክ መጠባበቂያ ክምችት ወጭ በማድረግ ለሚፈለገው የሰብዓዊ ድጋፍ ያውላል፤

፮/ በመንግስት ሲወሰን በየዓመቱ በሚደራጅ የመነሻ መረጃ መሠረት የአደጋ ምላሽ ድጋፍ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤

4/ Build a disaster-resilient national society by raising awareness and consciousness.

## 8. Head Office

The Head Office of the Commission shall be in Addis Ababa and may establish branch offices elsewhere in the country as may be necessary.

## 9. Powers and Duties of the Commission

The Commission shall have the following powers and duties:

1/ Initiate sectorial policies, strategies, legal frameworks and standards and implement the same when approved by the concerned body;

2/ Prepare and present to the Government annual national disaster risk management plan by collecting and coordinating from regions and lead sector institutions, and implement when approved ;

3/ Follow and, as necessary, provide support to lead sector institutions and private institutions for the integration and implementation of disaster risk reduction activities in their plans;

4/ Work in collaboration with relevant institutions to provide a response by organizing a multi-sectorial information system and profile about disaster risk management through conducting analysis and forecasting national early warning;

5/ When it is beyond the capacity of regions or when there is a call for support that is approved by the Commission, the Commission may provide support by withdrawing from its reserve and transporting; and when it is deemed necessary and decided by the government, it may withdraw from the strategic reserve on a replenishment basis and use it for the required humanitarian support;

6/ Provide and coordinate disaster response support as determined by the government based on the threshold information prepared annua›lly;

፯/ በፌደራል መንግስት ስልጣን ስር የሚወድቁ የአደጋ ሥጋት ቅነሳ፣ የአደጋ ምላሽ እንዲሁም መልሶ መቋቋም ፕሮግራሞችን ይቀርጻል፣ ያስተባብራል፣ ይከታተላል፣ ይገመግማል፤

7/ Design, coordinate, follow up and evaluate disaster risk reduction, response and rehabilitation programs that fall under the power of the federal government;

፰/ ከክልል እና ከመሪ ዘርፍ ተቋማት ጋር በመተባበር በሀገር አቀፍ ደረጃ የአደጋ ሥጋት መግለጫ ዝግጅትና በየጊዜው የማሻሻል ሥራን ይመራል፣ ያስተባብራል፤

8/ In collaboration with Regional States and sector authorities, lead and coordinate the development and regular updating of disaster risk profiles at the national level;

፱/ የአደጋ ሥጋት መግለጫን መሠረት በማድረግ የተሟላ የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓትን በየደረጃዉ ይዘረጋል፣ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣ የተዘረጋው ሥርዓት ተደራሽ፣ ለአደጋ ዝግጁነትና ምላሽ ዝግጁ እንዲሆን ያደርጋል፤

9/ On the basis of the disaster risk profile, develop and implement comprehensive early warning system and ensure it is accessible, responsive and disaster-ready;

፲/ ለድንገተኛ አደጋዎች የታቀዱ ዕቅዶች ተግባራዊ መሆን መቻላቸውን ለማረጋገጥ በየደረጃው በተከታታይ ወይም በዕቅድ ላይ ተመስርቶ የናሙና ልምምዶች እንዲከናወኑ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ የማስተካከያ እርምጃዎችንም ይወስዳል፣ እንዲወሰድም ያደርጋል፤

10/ Facilitate the conditions for regular and scheduled simulation exercises at all levels to assess plans for emergency preparedness are implemented accordingly, take and instruct to take corrective measures;

፲፩/ በቅድመ-አደጋ፣ በአደጋ እና በድህረ-አደጋ ወቅት የአደጋ ሥጋት ትንበያን ጨምሮ በአገር አቀፍ ደረጃ የሚካሄዱ ጥናቶችን ያጠናል፣ እንዲጠኑ ያደርጋል፣ ግምገማዎች እንዲካሄዱ ያደርጋል፣ ይመራል፣ ያስተባብራል፤

11/ Initiate, lead, and coordinate national-level studies and assessments before, during, and after a period of disaster, including disaster risk forecasts;

፲፪/ የፌደራል የቅድሚያ ማስጠንቀቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽ ማስተባበሪያ ማዕከል ሥራዎችን በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የተደገፈ በማድረግ ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ እንዳስፈላጊነቱም ተመሳሳይ ማዕከላት በክልል ደረጃ እንዲመሰረቱ ድጋፍ ያደርጋል፤

12/ Lead and Administer the tasks of the Federal Early Warning and Emergency Coordination Centre through the support of modern technology, and provide assistance as required for establishing similar centers at regional levels;

፲፫/ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር የድርጊት መርሀ-ግብርን ይቀርጻል፣ ይተገብራል፣ ክልሎች የራሳቸውን የአደጋ ስጋት ስራ አመራር የድርጊት መርሀ-ግብር እንዲቀርጹ ድጋፍ ያደርጋል፤

13/ Design and implement a disaster risk management plan of action; support regions in developing their own disaster risk management plans;

፲፬/ የመረጃ ኮሙዩኒኬሽን ቴክኖሎጂ ለአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥራ በስፋት ጥቅም ላይ እንዲዉል ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣ ድጋፍ ያደርጋል፣ በአገር ደረጃ የአደጋ

14/ Facilitate conditions and provide support for the wider application of information and communication technologies for disaster risk management; serve as a repository for disaster risk management

ሥጋት ሥራ አመራር የመረጃ ማዕከል ሆኖ ያገለግላል፤ እንዳስፈላጊነቱ ክልሎች ተመሳሳይ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ድጋፍ ያደርጋል፤

፲፭/ አደጋ የደረሰበትን ክልል ወይም ቦታ በተመለከተ አደጋ ስለመድረሱና ሃገራዊ ሥጋት መሆኑ የእወጃ የአሰራር ሥርዓት ይዘረጋል፤

፲፮/ ከሚመለከታቸዉ አካላት ጋር በመተባበር የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ሥርዓት በበጎ ፈቃደኞች የሚታገዝበትን አሠራር ሥርዓት ይዘረጋል፤ ሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፤

፲፯/ ከቀጠናዊ፣ አህጉራዊ እና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ ከመንግስትና መንግስታዊ ካልሆኑ ተቋማት ጋር የሥራ ግንኙነት ይፈጥራል፤ ይተባበራል፤ ትንበያዎችን፣ ቅድመ-ማስጠንቀቂያዎችን እና ከአደጋ ጋር የተያያዙ መረጃዎችን ከአገር ውስጥና ከዓለም አቀፍ አካላትና ድርጅቶች መረጃዎችን ይቀበላል፤ ጠቀሜታቸውን በመገምገም እንደየአስፈላጊነታቸው ያጋራል፤

፲፰/ ከፌደራል መሪ ዘርፍ ተቋማት፣ ከክልሎች፣ ከግሉ ዘርፍ እና ከሚዲያ ተቋማት ጋር በመተባበር ስለ አደጋ ስጋት፣ አደጋዎች ክስተትና ምላሽ ግንዛቤ ይፈጥራል፤ መረጃዎችን እና የጥንቃቄ መልዕክቶችን በቋሚነት ለህዝብ ያሳውቃል፤

፲፱/ ከፌደራል እና ከክልሎች እንዲሁም የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዘርፍ ሚና ያላቸው አካላት የሚሳተፉበት፣ የጥናትና ምርምር ውጤቶችና ትግበራዎች የሚቀርቡበት፣ ልምድ የሚለዋወጡበት አገር አቀፍ፤አህጉርና ዓለም አቀፍ የአደጋ ስጋት ቅነሳ መድረክ ያዘጋጃል፤ ልምዶች እንዲሰፉ ያደርጋል፤

፳/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሚመለከታቸው ተቋማት ጋር በመተባበር አገር-አቀፍ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ስልጠና ማዕከል ያደራጃል፤ በዘርፉ ላሉ ባለሙያዎች ደረጃ እና የሙያ ምስክር ወረቀት ይሰጣል፤

፳፩/ በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዙሪያ የሚሰሩ መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶችን ብቃታቸውን ያረጋግጣል፤ የሙያ ፈቃድ ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤ ይቆጣጠራል፤

information center at the national level and provide assistance to regions as needed for the establishment of similar centers;

15/ Establish rules of procedures for the declaration of disaster hit region or place as disaster area of national concern;

16/ In collaboration with the concerned bodies, establish and implement rules of procedure for volunteers to support disaster risk initiatives;

17/ Collaborate and establish working relationships with sub-regional, regional, and international organizations, as well as governmental and non-governmental institutions; receive and disseminate disaster risk information, forecasts, and early warning information from national and international bodies and organization share when it is necessary;

18/ In collaboration with the Federal and Regional sector institutions and the media, creat awareness about disaster risks and occurrences; disseminate information and precautionary messages to the public in a regular basis;

19/ Organize national, regional and international disaster risk reduction forums in which federal and regional as well as bodies having role in disaster risk management sector participate, findings and implementation of research and studies are presented, and share experiences ;

20/ Establish a national disaster risk management training center in partnership with key institutions as needed, and issue standard and professional certificates to professionals in the sector;

21/ Coordinate, supervise, issue professional license to non-governmental organizations working in areas of disaster risk management, and ensure their capacity;

፳፪/ ቅጽበታዊ አደጋዎችን ለመቆጣጠር የዘርፉን ሙያዊ አቅም ለማጎልበት የሚያስችሉ ተግባራትን ያከናውናል፤

፳፫/ የተለያዩ ዓለም አቀፍ ድርጅቶች ከመንግስት ጋር በገቡት ስምምነት መሠረት የአደጋ ስጋት ቅነሳ የልማት እና የሰብዓዊ ድጋፍ አቅርቦት ሥራቸውን በውጤታማነት መሥራት እንዲችሉ ይመራል፣ ያስተባበራል፣ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

፳፬/ በቅጽበታዊ እና የተራዘመ ጊዜ የሚወስዱ አደጋዎች ወቅት ለሰብአዊ ድጋፍ የሚውል የአስቸኳይ ጊዜ ምግብ እና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሳቁሶች በክምችት ይይዛል፣ ያስተዳድራል፤

፳፭/ የአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ ፣ በበላይነት ይመራል ፣ያስተባብራል፤

፳፮/ የስትራቴጂክ መጠባበቂያ ክምችት አገልግሎትን በበላይነት ይመራል፡ ያስተባብራል፤

፳፯/ የሰብዓዊ ድጋፍ የትራንስፖርት አገልግሎት ስርዓትን ይዘረጋል፣ በበላይነት ይመራል ፣ያስተባብራል፤

፳፰/ የእሳትና ሌሎች ቅጽበታዊ አደጋዎች አገልግሎትን በበላይነት ይመራል፣ ያስተባብራል፤

፳፱/ የሚመለከታቸው አካላት ማለትም መንግስት፣ ማህበረሰቡና በሰብዓዊነት ላይ የሚሰሩ ተቋማት ሙሉ ተሳትፎ ያደረጉበት የስጋት ተጋላጭነት መሠረት ያደረገ የአደጋ ተጎጅ የመለየት ስራ መከናወኑን ያረጋግጣል፤

፴/ በአደጋ ስጋት ገደብ ውሳኔ መሠረት የመመዘኛ መስፈርቶችን ለሚያሟሉ የአደጋ ስጋት ምላሽ ስራዎች ላይ ለሚሳተፉ አካላት ድጋፍ ያደርጋል፤

፴፩/ የአስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃ ይፋ ሲደረግ ኃብት የመመደብ፣ ድጋፍ የማሰባሰብና የማስተባበር ስራ ይሰራል፤

፴፪/ የንብረት ባለቤት ይሆናል፣ ውል ይዋዋላል፣ በስሙ ይከሳል፣ ይከሰሳል፤

፴፫/ የተቋቋመበትን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ሌሎች አስፈላጊ ተግባሮችን ያከናውናል።

22/ Perform tasks that enhance the sector's professional capacity to control disasters onset;

23/ Coordinate and provide the necessary support to the various international organizations for effective execution of their activities in areas of disaster risk reduction development and the provision of humanitarian support as agreed with the government;

24/ Reserve and administer food and non-food items necessary for humanitarian assistance in the event of sudden-onset and prolonged disasters;

25/ Administer and coordinate the Disaster Risk Response Reserve Fund;

26/ Administer and coordinate the Strategic Reserve Stock Service;

27/ Establish administer and coordinate the humanitarian aid transport system;

28/ Administer and coordinate the fire and other emergency disasters services;

29/ Ensures that vulnerability based targeting shall be conducted with the full participation of all stakeholders namely the government, the community, and the humanitarian operators;

30/ Provide support to those bodies that participate in disaster risk response works and fulfill the requirements based on the determination of disaster risk thresholds;

31/ Following the announcement of the declaration, the Commission shall engage in allocating, mobilizing and coordinating resources;

32/ Own property, enter into contract, sue and be sued in its own name;

33/ Undertake other activities necessary for the attainment of its objectives.

## ፲. የኮሚሽነሩ ሥልጣንና ተግባራት

፩/ የኮሚሽኑ ዋና ስራ አስፈፃሚ ሆኖ በምክር ቤቱ በሚሰጠው አጠቃላይ አቅጣጫ መሠረት የኮሚሽኑን ስራዎች ይመራል፤ ያስተዳድራል፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው አጠቃላይ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ኮሚሽነሩ፡-

ሀ) የኮሚሽኑን ተግባርና ኃላፊነት ሥራ ላይ ያውላል፤

ለ) ኮሚሽኑን ያደራጃል፤ የኮሚሽኑን ሠራተኞች በፌደራል ሲቪል ሰርቪስ ሕጎች መሠረት ይቀጥራል፤ ያስተዳድራል፤

ሐ) የኮሚሽኑን የሥራ ዕቅድና በጀት ያዘጋጃል፤ ሲፈቀድም በሥራ ላይ ያውላል፤

መ) ለኮሚሽኑ በተፈቀደ በጀትና የሥራ ዕቅድ መሠረት ገንዘብ ወጪ ያደርጋል፤

ሠ) ኮሚሽኑ ከሶስተኛ ወገኖች ጋር በሚያደርጋቸው ግንኙነቶች ሁሉ ኮሚሽኑን ይወክላል፤

ረ) የኮሚሽኑን የሥራ አፈፃፀም ሪፖርት አዘጋጅቶ በወቅቱ ምክር ቤቱን ጨምሮ ለሚመለከታቸው የመንግስት አካላት ያቀርባል፤

ሰ) ለኮሚሽኑ ሥራ ቅልጥፍና በሚያስፈልግ መጠን ከሥልጣንና ተግባሩ በከፊል ለኮሚሽኑ የስራ ኃላፊዎችና ሠራተኞች በውክልና ሊያስተላልፍ ይችላል፡፡

## ፲፩. የምክትል ኮሚሽነሮች ሥልጣንና ተግባራት

የኮሚሽኑ ምክትል ኮሚሽነሮች የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖራቸዋል፡-

፩/ በኮሚሽነሩ ተለይተው የተሰጡትን ሥልጣንና ተግባራት ያከናውናሉ፡፡

፪/ ኮሚሽነሩ በማይኖርበት ጊዜ ውክልና የተሰጠው ወይም በሹመት ቅድሚያ ያለው ምክትል ኮሚሽነር ኮሚሽነሩን ተክቶ ይሠራል፡፡

## 10. Powers and Duties of the Commissioner

1/ The Commissioner shall be the Chief Executive Officer of the Commission and shall oversee and administer the Commission's activities in accordance with the Council's general direction

2/ Without prejudice to the broad provision of Sub-Article (1) of this Article, the Commissioner shall have powers and duties to:-

a) Exercise the powers and duties of the Commission;

b) Organize the Commission, and hire and administer its employees in compliance with Federal Civil Service Laws;

c) Prepare the Commission’s activity plan and Budget, and implement when approved;

d) Make expenditure in conformity with the Commission’s approved Budget and work plan;

e) Represent the Commission in all its dealings with third parties;

f) Prepare and timely submit the Commission's performance report to the concerned government bodies, including the Council;

g) Delegate part of his powers to employees and officials of the Commission to the extent necessary to ensure the efficiency of the Commission.

## 11. Powers and Duties of the Deputy Commissioners

The Deputy Commissioners shall have the following powers and duties;

1/ Perform activities and powers specifically entrusted to them by the Commissioner

2/ In the Commissioner's absence, the Deputy Commissioner with power of attorney or the senior Deputy Commissioner shall represent and carry out the Commissioner's duties.

**፲፪. የምክር ቤቱ መቋቋም**

፩/ ምክር ቤቱ በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ የምክር ቤቱ ጽሕፈት ቤት ሆኖ ያገለግላል፡፡

**፲፫. የምክር ቤቱ አባላት**

፩/ ምክር ቤቱ የሚከተሉት አባላት ይኖሩታል፡-

ሀ) ጠቅላይ ሚኒስትሩ ወይም በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚወከል ሰው የምክር ቤቱ ……………………………….ሰብሳቢ፣

ለ) የክልል ርዕሳነ-መሥተዳድሮች ፣ የአዲስ አበባና የድሬዳዋ ከተማ ከንቲባዎች…… ……………………………….አባላት፣

ሐ) የመሪ የዘርፍ ተቋማት ኃላፊዎች ……………………………….አባላት፣

መ) የኢትዮጵያ ቀይ መስቀልና ጨረቃ ማህበር ኃላፊ ………………… አባል፣

ሠ) የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ጥምረት ኃላፊ ……………………………አባል፣

ረ) የኢትዮጵያ የሃይማኖት ተቋማት ጉባዔ ………………………………….አባል፣

ሰ) የኢትዮጵያ መገናኛ ብዙሃን ምክር ቤት ኃላፊ ………………………… አባል፣

ሸ. የኢትዮጵያ ንግድና ዘርፍ ማህበራት ምክር ቤት ……………………አባል፣

ቀ) ኮሚሽነሩ ………………አባልና ጸሃፊ፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ በኮሚሽኑ አቅራቢነት በጠቅላይ ሚኒስትሩ የሚሰየሙ ሌሎች አባላት ሊካተቱ ይችላሉ፡፡

**፲፬. የምክር ቤቱ ሥልጣንና ተግባራት**

ምክር ቤቱ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፡-

፩/ በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲና ስትራቴጂ ጉዳዮች ላይ የመቋቋም ብቃት ስትራቴጂና ፕሮግራሞችን ጨምሮ አጠቃላይ

**12. Establishment of the Council**

1/ The Council is hereby established by this Proclamation.

2/ The Commission shall serve as secretariat of the Council.

**13. Members of the Council**

1/ The Council shall have the following as its members:

a) The Prime Minster or the person delegated by him……….. Chairperson;

b) Heads of Regional States and Mayors of Addis Ababa and Dire dawa Administrative…………….. members;

c) Heads of lead sector institutions.. .. ……………………………..members;

d) Head of the Ethiopian Red Cross and Crescent ………………….... member;

e) Head of the Ethiopian Civil Society Council…………………..…… member;

f) Head of the Inter Religious Council of Ethiopia ……………………. Member;

g) Head of the Ethiopian Media Council ……………………………... member;

h) Ethiopian Chamber of Commerce and Sectorial Associations ........... member;

i) The Commissioner ...........Member and Secretary.

2/ Without prejudice to the provision of Sub-Article (1) of this Article, the Prime Minister may appoint other members upon the recommendation of the Commission.

**14. Powers and Duties of the Council**

The Council shall have the following powers and duties:-

1/ Provides overall leadership on disaster risk management policy and strategy issues; monitors and evaluates its performance;

አመራር ይሰጣል፣ አፈፃፀሙን ይከታተላል፣ ይገመግማል፣ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝም ፖሊሲውና ስትራቴጂው እንዲከለስ አቅጣጫ ያስቀምጣል፣

፪/ የአደጋውን መጠን እና ውስብስብነት መሠረት በማድረግ የፌደራል መንግስቱን ጣልቃ ገብነት የሚሻ አደጋ መከሰቱን ወይም የተከሰተው አደጋ መወገዱን ይፋ ያደርጋል፣

፫/ የስትራቴጅክ መጠባበቂያ ምግብና ምግብ-ነክ ያልሆኑ ቁሳቁስ የክምችት መጠን ይወስናል፣ እንደየአስፈላጊነቱ ለሰብዓዊ ድጋፍ ፣ለገበያ ማረጋጋት ፣ለኤክስፖርትና ለኢትዮጵያ ኤይድ ለመሳሰሉት በብድር የሚሰጥበትን ሥርዓት እንዲዘጋጅ ያደርጋል፣ መተግበሩንም ያረጋግጣል፣

፬/ የቅጽበታዊ አደጋዎች አገልግሎት ተቋማዊ አቅም እንዲጠናከር፣ የፓራሚሊተሪ የሰው ኃይል ስምሪት ሥርዓት እንዲደራጅና ውጤታማ እንዲሆን፣ የባለድርሻዎች ትብብርና ተሳትፎ እንዲጎለብት አመራር ይሰጣል፣

፭/ የአደጋ ስጋት የአስቸኳይ ጊዜ ምላሽንና የመሪ ዘርፍ ተቋማትን አካቶ ማቀድና መተግበርን በሚመለከት ኮሚሽኑ የሚያቀርበውን የውሣኔ ሀሳብ፣ አሰራርና ሥርዓቶችን በመመርመር ስራ ላይ እንዲውሉ ይወስናል፣ተጠያቂነትን ያረጋግጣል፣

፮/ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ውጤታማነትን ለማረጋገጥ የሚያስችሉ አህጉራዊና ዓለማቀፋዊ ትብብሮችና ግንኙነቶች እንዲፈጠሩ አቅጣጫዎችን ይሰጣል ፣ አተገባበራቸውንም ይከታተላል፣

፯/ የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ አጠቃቀምና አስተዳደር ሥርዓት መደራጀቱን ይከታተላል፣

፰/ ከኮሚሽኑ የሚቀርብለትን የተጠቃለለ እቅድና ሪፖርት መርምሮ ያፅድቃል፡፡

## ፲፭. ስለ ምክር ቤቱ ስብሰባ

፩/ ምክር ቤቱ በዓመት አራት ጊዜ መደበኛ ስብሰባውን ያደርጋል፣አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አስቸኳይ ስብሰባ ሊጠራ ይችላል፡፡

and, when necessary, sets direction for the revision of the policy and strategy;

2/ Declare the occurrence or removal of disasters that necessitate Federal Government intervention based on their scale of impact and complexity;

3/ Prepare a system and ensure the implementation of the provision of food and non-food items from the strategic reserve as needed through loan to humanitarian assistance, market stabilization, export, and Ethiopia Aid, and determine the quantity of the reserve;

4/ Provides leadership to strengthen the institutional capability of rapid onset emergency services; organize and make effective paramilitary personnel deployment system; enhances stakeholders cooperation and participation;

5/ Evaluate whether lead sector institutions are carrying out the activities entrusted to them by this Proclamation; deliberate on the Commission's recommendations on disaster risk emergency response practices and systems, as well as inclusive institutional planning and decide on their implementation;

6/ Provides directions for establishing continental and worldwide collaborations and relationships that may ensure the effectiveness of disaster risk management, and monitors their implementation;

7/ Follow the establishment of a system for the utilization and administration of the Ethiopian disaster risk response reserve fund;

8/ Evaluate and approve the consolidated report and plan submitted to it by the Commission.

## 15. Meeting of the Council

1/ The Council shall convene its regular meetings four times in a year, and may call extra-ordinary meeting as necessary.

፪/ ከግማሽ በላይ የምክር ቤቱ አባላት በስብሰባ ላይ ከተገኙ ምልዓተ-ጉባዔ ይሆናል፡፡

፫/ ምክር ቤቱ የራሱን የስብሰባ የሥነ-ሥርዓት መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

**፲፮. የኮሚሽኑ በጀት**

የኮሚሽኑ በጀት ከሚከተሉት የተውጣጣ ይሆናል፡-

፩/ ከመንግስት ከሚመደብ በጀት፤ እና

፪/ ከሰብዓዊ ድጋፍ ይሆናል፡፡

**፲፯. ግዥና የንብረት አስተዳደር**

አስቸኳይ ምላሽ የሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች እና የክምችት እጥረት ሲያጋጥም ኮሚሽኑ ግዥዎችን የገንዘብ ሚኒስቴር የግዥ አዋጁን መሠረት አድርጎ በሚያወጣው ልዩ መመሪያ መሠረት ይፈፅማል፡፡

**፲፰. ሒሳብ መዛግብት አያያዝ**

፩/ ኮሚሽኑ የተሟሉና ትክክለኛ የሆነ የሒሳብ መዛግብትን ይይዛል፡፡

፪/ የኮሚሽኑ የሒሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋናው ኦዲተር ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራል፡፡

**ክፍል ሶስት**

**ስለ የፌደራል መሪ ዘርፍ ተቋማት እና የክልል ተግባርና ኃላፊነት**

**፲፱. የመሪ ዘርፍ ተቋማት የወል ተግባርና ኃላፊነት**

መሪ የዘርፍ ተቋማት በሌላ ሕግ ከተሰጣቸው ሥልጣን በተጨማሪ ከአደጋ ስጋት ሥራ አመራር አንፃር የሚከተሉት የወል ተግባርና ኃላፊነት ይኖርባቸዋል፡-

፩/ መሪ ዘርፍ ተቋማት የበኩላቸውን ሚና እንዲወጡ የሚያስችላቸው የአደጋ ሥጋት ቅነሳ አሰራር ይዘረጋሉ፤ ውጤታማነቱን ያረጋግጣሉ፤

፪/ ተቋም ተኮር የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር እቅድና ፕሮግራም ያዘጋጃሉ፤ ይተገብራሉ፣ በአተገባበሩ ዙሪያም ለምክር ቤቱ ሪፖርት ያቀርባሉ፤

2/ A quorum shall be constituted if more than half of the Council Members are present.

3/ The Council may issue its own meeting rules of procedure.

**16. Budget of the Commission**

The Budget of the Commission shall be drawn from the following sources:

1/ Budget allocated by the Government; and

2/ Humanitarian supports.

**17. Procurement and Administration of Property**

In the event of an emergency situation and a shortage of reserves, the Commission may conduct procurements in line with special regulations to be issued by the Ministry of Finance based on the Procurement Proclamation.

**18. Books of Accounts**

1/ The Commission shall keep complete and accurate books of accounts.

2/ The Commission's books of accounts and financial documents shall be audited annually by the Auditor General or an Auditor assigned by it.

**SECTION THREE**

**RESPONSIBILITIES AND DUTIES OF LEAD SECTOR OFFICES AND REGIONS**

**19. Common Responsibilities and Duties of Lead Sector Institutions**

Without prejudice to the powers and duties under their respective establishing laws, lead sector institutions shall have the following common responsibilities and duties in regard to disaster risk management

1/ Establish system within its institution to carry out its role of disaster risk reduction and management, and ensure its effectiveness;

2/ Prepare and implement sector-specific disaster risk management plans, and submit performance reports to the council;

፫/ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር በተቋማዊ የስራ ዝርዝር፣ በፖሊሲዎቻቸዉና በልማት ዕቅዳቸው ውስጥ መካተቱን ያረጋግጣሉ፤

፬/ ከመሪ ዘርፍ ተቋማት ጋር በሚገናኙ የአደጋ ስጋቶች ዙሪያ ግንዛቤ እና ትምህርት ይሰጣሉ፤

፭/ የአደጋ ስጋት ሥራ አመራርን አስመልክቶ በዘርፉ የሚሰሩ የመንግስት፣ የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች፣ የግል ተቋማት፣ የሰብዓዊና የልማት አጋሮችን ተሳትፎ ያረጋግጣሉ፤ ያቀናጃሉ፤ ያስተባብራሉ፤

፮/ የዘርፉን የቅድመ-ማስጠንቀቂያ መረጃ አሰባሰብን፣ትንተናን፣ትንበያንና ሥርጭትን በሚመለከት ለአገራዊ የአደጋ ስጋት ሁኔታዎች መግለጫ ከኮሚሽኑ ጋር ይተባበራሉ፤

፯/ በዘርፋቸው ሊከሰቱ የሚችሉ ቅጽበታዊ አደጋዎችን በሚመለከት ተገቢውንና የተሟላ ዝግጅት ያደርጋሉ፤ሲከሰትም ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ፈጣን ምላሽ ይሰጣሉ፤

፰/ በዚህ አዋጅ እና በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲው ላይ የተመለከቱትን የተናጠል ተግባርና ኃላፊነት በተጠያቂነት መርህ ይፈፅማሉ፡፡

## ፳. የመሪ ዘርፍ ተቋማት የተናጠል ተግባርና ኃላፊነት

መሪ ዘርፍ ተቋማት የሚከተሉት የተናጠል ኃላፊነትና ተግባር ይኖራቸዋል፡-

፩/ የግብርና ሚኒስቴር፡- የግብርና ነክ አደጋ አምጪ ክስተቶች ማለትም የእንስሳት በሽታን እና የሰብል እህሎችና የሆልቲ-ካልቸር አደጋን እንዲሁም የእንስሳት መኖ እና ሰብል አቅርቦትን በተመለከተ እንዲሁም የተራቆቱ ወይም ለአደጋ የተጋለጡ የተፈጥሮ ሀብትን መሬት፣ አፈር፣ ውሃ፣ ደን፣ እንዲያገግሙ ለማድረግ፣ የደኖች እና ቁጥቋጦዎች እሳት፣ድንበር ዘለል የግብርና አደጋ ስጋቶች ለመከላከልና ስጋት ለመቀነስ እንደ መሪ የዘርፉ ተቋም ሆኖ ያገለግላል፤

3/ Ensure that disaster risk management is mainstreamed in their institutional job description, policies and development plans;

4/ Provide public awareness and education on disaster risks related to lead sector institutions;

5/ In relation to disaster risk management, collaborate, coordinate and lead the activities of governmental, civil society organizations, private institutions, humanitarian and development partners private, government and humanitarian development partners working in the sector, and ensure their participation;

6/ Collaborate with the Commission on the collection, analysis, forecast and dissemination of early warning information on the national disaster risk situation;

7/ Perform appropriate and complete preparedness In their sectors regarding possible emergency disasters, when occurred provide immediate response in collaboration with concerned bodies;

8/ Execute in an accountable manner the joint and individual responsibilities provided under this Proclamation and the Disaster Risk Management Policy.

## 20. Individual Responsibilities and Duties of Lead Sector Institutions

Lead sector institutions shall have the following individual responsibilities and duties:

1/ Ministry of Agriculture፡ shall act as a lead sectoral institution in relation to agriculture-related hazards such as livestock diseases and crop pests and diseases, as well as disaster-induced shortages of animal feed and crop seed supply, and for the rehabilitation of degraded or vulnerable natural resources such as land, soil, water, forest, and preventing and reducing forest and bush fires;

፪/ የጤና ሚኒስቴር፡- በምግብ እጥረት ምክንያት ለሚደርስ ህጻናትን እና እናቶችን የሚያጠቃ የሥርዓተ-ምግብ ችግር እንዲሁም ወረርሽኝ ጋር የተያያዙ አደጋዎችን በተመለከተ እንዲሁም በአደጋ ለተፈናቀሉና መጠለያ ውስጥ ለሚገኙ ተረጅዎች የጤና አገልግሎት በመስጠት፤ የሥነ-ልቦና ድጋፍ በመስጠት በማስተባበር መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፫/ የዉሃ እና ኢነርጂ ሚኒስቴር፡- ከጎርፍ እና ዉሃ አቅርቦት እንዲሁም ከዉሃ ግድብ መሙላት ጋር የሚገናኝ አደጋዎችን በተመለከተ መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤ ሚንስቴሩ የስነ-አየር፤ ስነ-ዉሃ እና ስነ-ዉቅያኖስ አደጋዎችን በተመለከተ ትንተና፤ ትንበያ፤ ቅድመ -ማስጠንቀቂያ እንዲሁም ስነ ምህዳራዊ ስርጭታቸውን ጋር በተገናኘ አለምአቀፍ ትብብር ያድርጋል እንዲሁም በአደጋ ለተፈናቀሉ እና መጠለያ ዉስጥ ለገቡ ተጎጅዎች የዉሃ አቅርቦት አገልግሎት ይሰጣል፤ ያስተባብራል፤

፬/ የሰላም ሚኒስቴር፡- ከሰላም ግንባታና ከግጭት ቅድመ ማስጠንቀቂያና ምላሽ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በተመለከተ መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፭/ የትንራንስፖርት እና ሎጅስቲክ ሚኒስቴር፡- ከትራንስፖርት አገልግሎት እና የመሰረተ-ልማት ጋር የተገናኙ አደጋዎችን በተመለከተ መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፮/ የማዕድን ሚኒስቴር፡- የሥነ-ምድር አደጋዎችን እንደ ርእደ መሬት፤ እሳተ ገሞራ፤ የመሬት መንሸራተት እና የመሰሉ ስነ-ምድራዊ የሆኑ አደጋዎችን በመለየት የሥጋት ተጋላጭነትን ለመቀነስ ከጂኦሎጂካል ተቋማት የሚሠራውን ሥራ በማስተባበር ረገድ መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል

፯/ የመከላከያ ሚኒስቴር፡- ከፍተኛ የሰው ሰራሽና የተፈጥሮ የአደጋ ክስተት ሲያጋጥም የሚጠፉ ወገኖችን የመፈለግና ህይወታቸውን የማትረፍ፣ ስርዓት በማስከበር መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፰/ የከተማና መሠረተ ልማት ሚኒስቴር፡- ከተማ ልማት እና ህንጻ ግንባታ ጋር የተገናኙ የእሳት እና የህንጻ መደርመስ አደጋዎችን

2/ Ministry of Health፡ shall act as a lead sectoral institution in terms of food shortage-induced malnutrition affecting children and mothers, as well as other human epidemics associated with disasters, and shall provide or coordinate the provision of health services, psychological support to those displaced by disaster and found in shelters;

3/ Ministry of Water and Energy፡ shall act as a lead institution in responding to floods and other water supply dangers, as well as dam overflows and associated disasters; it shall also be responsible for international cooperation in the observation, assessment, forecast, warning, and identification of levels of natural disaster risks in meteorological, hydrographic, and oceanographic aspects, as well as providing or coordinating the provision of water supply to displaced people that live in shelters.

4/ Ministry of Peace:- shall act as a lead institution in relation to peace building and conflict early warning and responses.

5/ Ministry of Transport and Logistics፡ shall act as lead sector institution with respect to transport service infrastructure-related hazards.

6/ Ministry of Mines shall act as a lead sector institution in identifying geological disasters such as earthquakes, volcanoes, landslides, and related disasters so as to reducing risk vulnerability, as well as coordinating its work with geological institutions.

7/ Ministry of Defense shall act lead sector institution in searching for disappeared people, saving their lives and securing orders in the event of a severe manmade and natural disaster.

8/ Ministry of Urban and Infrastructure shall be a lead sector institution in urban infrastructure and building construction-related hazards and disasters, such as fire

በተመለከተ እንዲሁም በአደጋ ለተፈናቀሉ ዜጎች እንደ አስፈላጊነቱ የጊዜያዊ መጠለያዎች ግንባታን በማከናወን እና በማስተባበር መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፱/ የትምህርት ሚኒስቴር፡- ቅድመ-አደጋ፤ በአደጋ ጊዜ እንዲሁም ድህረ-አደጋ ወቅት እና የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ጉዳይ ከቅድመ መደበኛ እስከ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በስርአተ-ትምህርት፤ በጥናትና ምርምሮች ዉስጥ መካተቱን በተመለከተ አስፈላጊ እርምጃዎችን ለመዉሰድ መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፲/ የዉጭ ጉዳይ ሚኒስቴር፡- ኮሚሽኑ ወይም ምክር ቤቱ የአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ጉዳዮችን በተመለከተ ከውጭ ሀገር መንግሥታትና ከዓለም አቀፍ ድርጅቶች ጋር የሚያደርጓቸውን ሁሉንም ግንኙነቶች ያስተባብራል፤

፲፩/ የፕላንና ልማት ሚኒስቴር፡- በአገራዊ እቅዶችና ፕሮግራሞች ውስጥ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና ቅነሳ አገራዊና ሴክተራል እቅዶች ላይ መካተቱን ያረጋግጣል፤ እንዲካተቱ ያስተባብራል፤ አፈፃፀሙን ይከታተላል፤ የአየር ንብረት ለውጥ እና የአካባቢ ብክለት ጠንቆችና ተዛማጅ አደጋዎችን በሚመለከት የማጣጣምና የማላመድ ስልቶችን በመዘርጋትና በማስተግበር እንደ መሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ያስተባብራል፤

፲፪/ የገንዘብ ሚኒስቴር፡- የአደጋ ስጋት ቅነሳ ስልቶችን መሰረት ባደረገ አግባብ ለሚቀርቡ የልማት ዕቅዶች ላይ አስፈላጊው የፋይናንስ አቅርቦት፣ የአደጋ ስጋትን ታሳቢ ያደረገ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ፋይናንስ እና የመድን ሥርዓት የመዘርጋት፣ የመቆጣጠርና የማስተባበር ተግባራትን ይመራል፤

፲፫/ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር፡- የአደጋ ሰለባ ለሆኑ ሴቶች ፤ ወጣቶች፤ ሕጻናት፣ አካል ጉዳተኞች፤ አረጋውያንና ሌሎች የማህበረሰብ ክፍሎችን የመንከበከብና የመጠበቅ እንደ መሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ይሰራል፤

and building demolition, and shall coordinate the construction of temporary shelters for people affected by the disaster.

9/ Ministry of Education shall be a lead sector institution in taking the necessary measures to mainstream disaster risk management at the time of pre-disaster, during disaster, and post-disaster into school curricula and integrating them into studies and researches of pre-regular to higher educational institutions.

10/ Ministry of Foreign Affairs: shall coordinate all of the Council's or Commission's relationships with foreign states and international organizations regarding Disaster Risk Management.

11/ Ministry of Planning and Development: ensures that disaster risk management and reduction are included in national and sectorial plans and programs, coordinates their inclusion, and monitors their implementation; as lead sector institution coordinate climate change and environmental pollution-related disasters and dangers by developing alignment and adaption strategies

12/ Ministry of Finance: shall provide the necessary funding for development plans based on disaster risk reduction strategies; it shall also establish disaster risk financing and insurance systems that take disaster risk into account, as well as lead, coordinate, and supervise the activities thereof

13/ Ministry of Women and Social Affairs:- shall act as lead sector institution for providing care and protection to women, youth, children, people with disabilities, the elderly, and other sectors of the society who have been affected by disaster.

፲፬/ የመንግስት ኮሙዩኒኬሽን አገልግሎት፡- ከአደጋ በፊት፣ በአደጋ ጊዜና ከአደጋ በኋላ መወሰድ በሚገባቸው አዎንታዊ እርምጃዎች ላይ ግንዛቤ መፍጠር፣ ለተጎጅዎች የሚደረገውን የጥንቃቄ እርምጃ ማሳወቅ ፣ በመንግስትና በአጋር አካላት የሚያስፈልገውንና የተደረገውን የድጋፍ ዓይነትና መጠን ለማሳወቅ እንደ መሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ይሰራል፤

፲፭/ የንግድና ቀጠናዎች ትስስር ሚኒስቴር፡- የአደጋ ስጋትን ለመቀነስ የጥራት ደረጃዎችን የማስጠበቅና የመቆጣጠር፣ ከአደጋዎች መከሰት ጋር በተያያዘ በምግብና ምግብ ነክ ባልሆኑ ቁሳቁሶች ዋጋ ላይ የሚፈጠረውን ሰው ሰራሽ የዋጋ ንረት የመቆጣጠር እና የተረጋጋ ገበያ እንዲኖር ለማድረግ እንደመሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ይሰራል፤

፲፮/ መስኖና ቆላማ አካባቢዎች ልማት ሚኒስቴር፡- ለድርቅ ተጋላጭ የሆኑ ቆላማና የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎችን ልማት በሚመለከት የሚኖሩ የአደጋ ስጋቶችን ለመቅረፍ እንደመሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ይሰራል፤

፲፯/ ባህልና ስፖርት ሚኒስቴር፡- የአደባባይ ክብረ በዓል በሚከበርባቸው አደባባዮች፣ አደራሾች፣ ስቴዲዮሞች እና የስፖርታዊ ኩነቶች በሚደረጉበት ወቅት ከአደጋ ስጋት ነፃ እንዲሆኑ ማድረግ እንዲሁም አደጋዎች እንዳይፈጠሩ የማስተባበር ሚና ይኖረዋል፤

፲፰/ ቱሪዝም ሚኒስቴር፡- በአገራችን በተለያዩ ደረጃ ለሚገነቡና ትላልቅ ዓለማቀፋዊ፣ አህጉራዊና አገራዊ ኩነቶች ለሚያስተናግዱ ሆቴሎች፣ የመዝናኛ ቦታዎች እና የኩነት ማስተናገጃ ቦታዎች ስታንዳርዶችን በማዘጋጀት በማስተግበርና በመቆጣጠር የአደጋ ስጋት ቅነሳ ተግባራትን በማከናወን መሪ የዘርፍ ተቋም ይሆናል፤

፲፱/ የስራና ክህሎት ሚኒስቴር፤- በምግብ ዋስትና እና በስራ አጥነት ውስጥ ለሚኖሩ ዜጎች የኑሮ መሠረትና የስራ ዕድል በመፍጠር ፤ስልጠና በመስጠት ፤ብድርና የመስሪያ ቦታ በማመቻቸት፤ ፈጠራን በማበረታታት፤ የተፈናቀሉና በካምፕ የሚኖሩ ዜጎችን ምርታማ እንዲሆኑ የክህሎት ስልጠና

14/ Government Communication Services:- shall act as lead sector institution in raising awareness about the positive steps that should be taken before, during, and after a disaster, informing victims of the precautionary measures being taken, and communicating the type and amount of assistance required and provided by the government and partner agencies.

15/ Ministry of Trade and Regional Integration:- shall act as lead sector institution for maintaining and monitoring quality standards so as to reduce disaster risk; it shall also act as the lead sector institution for controlling artificial price increases in food and non-food items that are related with disaster events, as well as ensuring market stability.

16/ Ministry of Irrigation and Lowland:- shall act as the lead sector institution for addressing disaster risks related to the development of drought-prone lowland, pastoral, and semi-pastoral areas

17/ Ministry of Culture and Sport:- shall have a coordinating role in terms of ensuring that public celebrations, venues, stadiums, and sporting events are disaster-free and prevent disasters from occurring.

18/ Ministry of Tourism: shall act as the lead sector institution in developing, implementing, and monitoring standards for hotels, resorts, and event venues that are being built at various levels and hosting major international, continental, and national events in Ethiopia, as well as carrying out disaster risk reduction activities

19/ Ministry of Labor and Skills;- shall act as a lead institution in reducing disaster risks and vulnerability by providing livelihoods and employment opportunities for citizens living in extreme food insecurity and unemployment, providing training, facilitating loans and housing, encouraging

በመስጠት የዜጎችን የአደጋ ስጋትና ተጋላጭነትን በመቀነስ መሪ የዘርፉ ተቋም ይሆናል ፡፡

፳/ የፍትህ ሚኒስቴር፡- ከአደጋ ስጋት ሥራ ጋር ተያያዥነት ያላቸውን ዓለም አቀፋዊ፣ አህጉራዊ እና ቀጠናዊ ስምምነቶችንና ፕሮቶኮሎችን ከሃገሪቱ ሕጎች ጋር መናበባቸውንና መተግበራቸውን ያረጋግጣል ፤ በአደጋ ሥጋት ሥራ አመራር ፖሊሲ ትግበራ ወቅት ተጠያቂነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ሕጎች እንዲወጡና እንዲተገበሩ ያደርጋል፡፡

፳፩/ ፌደራል ፖሊስ፡- በአደጋ ጊዜ የተለያዩ የፎረንሲክ ምርመራ ስራዎችን፣ የነፍስ አድን ስራዎችን በማከናወን እና በአደጋ አካባቢዎች ቀድሞ በመድረስና በመቆጣጠር ፣ የፀጥታ ስራዎችን በማረጋገጥ ተጨማሪ ጉዳቶች እንዳይደርሱ የመከላከልና የሰብዓዊ ድጋፎች በትክክል ለተጠቃሚው እንዲደርሱ የማድረግ ሥራ ይሰራል፡፡

፳፪/ ብሔራዊ የመረጃና ደህንነት አገልግሎት፡- ከአደጋ ስጋት ተጋላጭነት ለመከላከል ፤ ለማቅለልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል ከብሔራዊ ደህንነት ጋር የተያያዙ መረጃዎች በመሰብሰብ ፣ በመተንተን እና በማቅረብ መሪ የዘርፍ ተቋም ሆኖ ይሰራል፡፡

## ፳፩. የክልል ተግባርና ኃላፊነት

ክልሎች የአደጋ ስጋት ስራ አመራርን በተመለከተ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖራቸዋል፡-

፩/ ከዚህ አዋጅ ጋር የተጣጣመ የየራሳቸው የአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ማዕቀፍ፣ ስልት እና ሕግ መቅረፅ፤

፪/ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ዕቅድና ፕሮግራሞቻቸውን ከኮሚሽኑ ጋር ማቀናጀት፤

፫/ ከኮሚሽኑ በዓይነትና በገንዘብ የተመደበላቸው ሁሉም ክልሎች፡-

ሀ) ለሰብዓዊ ድጋፍ የተላኩ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ድጋፎች አጠቃቀም ሪፖርት በወቅቱ መላክ፤

ለ) ገንዘብና ሀብት አጠቃቀም የሚያሳይ የሂሳብ እና የኦዲት ሪፖርት በሥራ ላይ ባሉና ተቀባይነት ባላቸው የሂሳብ መመዘኛዎች መሠረት ማቅረብ፡

innovation, and providing skills training to displaced and camp-dwelling citizens to be productive.

20/ Ministry of Justice: Ensures that international, regional and local conventions and protocols related to disaster risk management are read and implemented in accordance with national laws; Ensures that laws are enacted and implemented on matters related to liability during the implementation of disaster risk management policies.

21/ Federal Police: - In times of emergency, it carries out various forensic investigations, rescue operations, and early arrival and control in disaster areas, ensuring security operations, preventing further damage, and ensuring that humanitarian aid reaches the beneficiaries properly.

22/ National Intelligence and Security Service: - Acts as a leading sector institution by collecting, analyzing, and providing information related to national security to prevent, mitigate, and respond to threats.

## 21. Powers and Duties of Regions

Regions shall have the following powers and duties regarding disaster risk management:

1/ Enact their own disaster risk reduction and management framework, strategy and laws compatible with this Proclamation

2/ Integrate their disaster risk management plans and programs with those of the Commission

3/ All regions to which the Commission provides in-kind and financial allocations:

a) Promptly submit their reports on the utilization of food and non-food items they received;

b) Submit financial reports prepared according to accepted accounting rules and showing the utilization of the funds and resources.

፬/ የአስቸኳይ የአደጋ ሥጋት ዳሰሳ ጥናት ለማድረግና የመከላከያ እርምጃዎችን ለመውሰድ ከአካባቢያዊ ከአጎራባች ክልሎች አስተዳደሮችና ማህበረሰቦች ጋር አጋርነትን ማጠናከርና መደገፍ፤

፭/ ተቀባይነት ያላቸው የአደጋ ሥጋት ግንዛቤና ትምህርት መሰጠቱን ማረጋገጥ፤

፮/ የሰብዓዊ ድጋፍ አሰጣጡ በኃላፊነትና በተጠያቂነት መርህ ላይ ተመስርቶ የልየታና የሥርጭት ስራ መሰራቱን ማረጋገጥ፤

፯/ በክልላቸው ለአደጋ ስጋት አይበገሬነትን ለማረጋገጥ የሚያስችለውን የቅድመ ማስጠንቀቂያ እና ምላሽ ሥርዓት ተግባራዊ መሆኑን ማረጋገጥ

፰/ ለአደጋ ስጋት ምላሽ እና የበጎ ፈቃደኝነት አገልግሎት ስርዓትን መዘርጋትና መተግበር፤

፱/ የመጠባበቂያና የአስቸኳይ ጊዜ ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ የክምችት ተቋምና የአደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ በማቋቋም በአደጋ ስጋት ገደብ መሠረት የሰብዓዊ ድጋፍ ፍላጎትን በክልል አቅም መሸፈን፡፡

## ክፍል አራት

## ስለ የአደጋ ስጋት ገደብ፣ አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃ እና የኢትዮጵያ እሳት ኮድ

### ፳፪. ስለ የአደጋ ስጋት ገደብ

፩/ የአደጋ ስጋት ደረጃ ገደብ ምክር ቤቱ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት የሚወሰን ሆኖ የአደጋ ሥጋት ደረጃ ጥልቀት፣ ስፋት፣ ክብደት፣ የአደጋውን ኃይል፣ የተፅዕኖ ወሰን፣ በሰው ሕይወትና ንብረት ላይ ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት፤ በየደረጃው የሚገኘው የአስተዳደር እርከን አደጋውን የመመለስ አቅሙ፤የሚያስተዳድረው የሕዝብ ቁጥር የመሳሰሉትን መመዘኛ መስፈርቶች ከግምት ውስጥ በማስገባት የሚወሰን ይሆናል፡፡

፪/ የአደጋ ስጋት ገደብ መስፈርት የተፈጥሮና የሰው ሰራሽ አደጋዎች ሚዛን መሠረት በማድረግ በጥናት ላይ ተመስርቶ የሚወሰን ይሆናል፡፡

4/ Strengthen and support partnerships with among regions, local administrations and communities to undertake emergency risk assessments and mitigation measures;

5/ ensuring the provision of appropriate disaster risk awareness and education;

6/ Ensure the identification, distribution and provision of humanitarian support activities are conducted based on the principles of transparency and accountability;

7/ Establish and implement in their region system of early warning that ensures resilience;

8/ Establish and implement disaster response system and voluntary services for resilience building and humanitarian assistance;

9/ Cover humanitarian needs using regional capacity in accordance with disaster risk threshold by establishing institutions of food and non-food reserve and disaster risk reserve fund.

## SECTION FOUR

## DISASTER RISK THRESHOLD, DECLARATION OF EMERGENCY AND FIRE CODE

### 22. Disaster Risk Threshold

1/ The disaster risk threshold which shall be determined by a Regulation to be issued by the Council shall take in to account the intensity, breadth, severity, strength of the disaster, scope of effect, possible damage to human lives and property, capacity of administrative bodies at every level to prevent the disaster, condition of surplus productivity, number of population, and related evaluation measures.

2/ The requirements for disaster risk threshold shall be determined based on the studies of the scale of natural and manmade disaster

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው የአደጋ ስጋት ገደብ በታች የሆነ የአደጋ ክስተት ሲፈጠር ክልሎች የተፈጠረውን አደጋ በራሳቸው አቅም የመከላከል፣ የመዘጋጀት፣ ምላሽ የመስጠት እና መልሶ የማቋቋም ኃላፊነት አለባቸው፡፡

፬/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ከተወሰነው የአደጋ ስጋት ገደብ በላይ መሆኑ ሲረጋገጥ የሚቀጥለው ክልላዊ የበላይ አስተዳደር እርከን እና የፌደራል መንግስቱ እንደ ቅደም ተከተላቸው ምላሽ ይሰጣሉ፡፡

**፳፫. ስለ አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃ**

፩/ አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃን በተመለከተ አደጋው ከመደበኛው የዝግጁነት ደረጃ ከክልሎች አቅም በላይ ሆኖ በተገኘ ጊዜ በኮሚሽኑ አቅራቢነት በምክር ቤቱ በኩል ይፋ ይደረጋል፡፡

፪/ ከላይ የተመለከተው ቢኖርም ቅጽበታዊ አደጋ ሲከሰትና ምክር ቤቱም ሊሰበሰብ የማይችል ከሆነ ጠቅላይ ሚኒስትሩ አደጋውን ይፋ ሊያደርግ ይችላል፡፡

፫/ ምክር ቤቱ የሰው ስራሽ እና የተፈጥሮ አደጋዎችን ደረጃ በመገምገም አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃ የሚደነገገበት አሰራር ይዘረጋል፡፡

፬/ አስቸኳይ የአደጋ ጊዜ እወጃ የአገር ውስጥ ሁለንተናዊ አቅምን ለማነቃቃት፤ ባለድርሻዎችን ለማስተባበር፤ ግዴታዎችን ለማስቀመጥ፤ ጉዳቶችን ለመቀነስና የህዝብን ግንዛቤ በሚያጎለብት ሁኔታ ተፈፃሚ ይደረጋል፡፡

**፳፬. የኢትዮጵያ እሳት ኮድ**

፩/ የኢትዮጵያ እሳት ኮድ የሚከተሉትን ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

ሀ) ነዋሪዎች እና ዜጎች ሕይወታቸውንና ንብረታቸውን እንዲሁም የልማት አውታሮች ደህንነት ከማንኛውም ዓይነት የእሳት አደጋዎች እንዲጠበቅ ለማድረግ፣ ማናቸውም መንግስታዊ፤ መንግስታዊ ያልሆኑ እና የግል ተቋማት ደህንነታቸው ተጠብቆ አስተማማኝ የስራ አካባቢ ለመፍጠር፤

3/ In situations where the disaster is below the threshold stated under Sub-Article (1) of this Article, Regions shall have the responsibility to use their own capacity to prevent, prepare, respond and rehabilitate the disaster.

4/ The next Higher Regional Authority and the Federal Government, respectively, shall respond to a disaster which is beyond the threshold mentioned under Sub-Article (1) of this Article.

**23. Declaration of Emergency**

1/ Declaration of emergency disaster shall be made by the Council upon submission by the Commission and when the disaster is beyond the capacity of the region and cannot be addressed by the regular preparedness level.

2/ Notwithstanding the above, the Prime Minister may declare the state of emergency disaster where there is rapid onset disaster and the Council is not in a position to convene.

3/ The Council may establish a system of declaration of emergency disaster by assessing level of manmade and natural disaster.

4/ Declaration of emergency shall be executed in consideration of mobilization of overall local capacity, coordination of stakeholders, set obligations, reduce damages and raise public awareness.

**24. The Ethiopian Fire Code**

1/ The Ethiopian Fire Code shall have the following objectives፡

a) To protect the lives and property of residents and citizens and the safety of development infrastructures from any fire hazards and to create a safe working environment for any governmental, non-governmental and private institutions;

ለ) ማንኛውም የህዝብ መገልገያ ሕንፃ ተቀባይነት ባለው የእሳት አደጋ ደህንነት መከላከያ መስፈርት መሠረት የእሳት አደጋን ሊቋቋም እና አደጋ ቢከሰትም በተጠቃሚዎችና በአካባቢው ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ሊቀንስ በሚችል መልኩ ጥቅም ላይ መዋሉን ለማረጋገጥ፤

ሐ) በአገልግሎት መስጫ ሕንፃዎች የአደገኛ ቁሶች አያያዝ፤ አደረጃጀት እና አጠቃቀም ከሕንፃው የእሳት ደህንነት መስፈርት መሠረት መሆኑን ለማረጋገጥ፤

መ) የእሳት አደጋ ደህንነት መፈተሻ መሣሪያዎች አያያዝና አጠቃቀም ዝቅተኛ የእሳት አደጋ ደህንነት መስፈርቱን ያሟሉ ስለመሆኑ ለማረጋገጥ፤

፪/ የኢትዮጵያ የእሳት ኮድ በሚከተለው መልኩ ይተገበራል፡-

ሀ) የኢትዮጵያ የእሳት ኮድ የዜጎችን ሕይወትና ንብረት እንዲሁም የልማት አውታሮችን እና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማትን ደህንነት ለማስጠበቅ ዝርዝር የተለያዩ የእሳት መከላከያ እና መቆጣጠሪያ ስታንዳርዶችን የያዘና እንደ ሃገር ወጥነት ባለው መልኩ የሚተገበር ይሆናል፡፡

ለ) የኢትዮጵያ የእሳት ኮድ በኢትዮጵያ እሳትና ሌሎች ድንገተኛ አደጋዎች አገልግሎት እና በተዋረድ በሚገኙት የዘርፉ ተቋማት አስፈፃሚነት ተግባራዊ ይሆናል፡፡

ሐ) የኢትዮጵያ የእሳት ኮድ ዝርዝር አተገባበር በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ የሚወሰን ይሆናል ፡፡

## ክፍል አምስት
## ስለ አደጋ ተጎጂዎች እና ተጋላጮች መብት እና ግዴታ

### ፳፭. የአደጋ ተጎጂዎች እና ተጋላጮች መብት

የአደጋ ተጎጂዎች እና ተጋላጮች የሚከተሉት መብቶች ይኖሯቸዋል፡-

b) To ensure that any building providing public service shall be used having acceptable fire hazard safety standards that can resist the effects of fire hazard and minimize the damages on the people and the environment;

c) To ensure whether the handling, organization and usage of hazardous materials are according to the safety standards of the building;

d) To ensure that the handling and usage of fire hazard detecting equipment meet the minimum fire hazard safety standards.

2/ The Ethiopian fire code shall be implemented as follows:

a) The Ethiopian fire code shall be implemented consistently at the national level having different detail fire protection and control standards to protect the lives and property of citizens as well as development infrastructures and institutions of service providers.

b) The Ethiopian fire code shall be implemented by Ethiopian fire and other emergency disaster service and by sector institutions found hierarchically.

c) Details of the operation of the Ethiopian fire code shall be determined by a Regulation to be issued by the Council of Ministers

## SECTION FIVE
## RIGHTS AND DUTIES OF VICTIMS AND VULNERABLE PEOPLE TO DISASTER

### 25. Rights of Vctims and Vulnerable People to Disaster

Victims and vulnerable people to disaster shall have the following rights:

፩/ ሕጋዊ በሆነ አካል የሚወጡ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር መረጃዎችን የማግኘት፤

፪/ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር እና ቅነሳ በተመለከተ የዕቅድ ሥራ ውስጥ የመሳተፍ፤ ማህበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ክህሎት መር የስራ ዕድል ፈጠራ ፕሮግራሞች ላይ በንቃት የመሳተፍ፤

፫/ በተግባቦት እና በትምህርት መርሃ-ግብሮች ውስጥ የመሳተፍ እና ካሉበት ነባራዊ ሁኔታ አንፃር ስለ አደጋ ስጋት መከላከልና ዝግጁነት ዕውቀታቸውን የማዳበር፤

፬/ የአደጋ ጉዳት ከአቅም በላይ ሲሆን በሕግ መሠረት ለተወሰነ ጊዜ እስኪቋቋሙ ድረስ የአገሪቱ አቅም በፈቀደ መጠን ሰብዓዊ ድጋፍ የማግኘት፤

፭/ አደጋን በመከላከልና በመቆጣጠር ማህበረሰቡን በማገዝ የመሳተፍ፤ በተለይም የበጎ አድራጎት ተግባራት ላይ በነፃና በፍቃደኝነት የመሳተፍ፤

፮/ አቅማቸው በፈቀደ መጠን አደጋን ለመከላከልና ለመቆጣጠር የሚያስችሉ ተግባራት ላይ በንቃት የመሳተፍ፤

## ፳፮. <u>የአደጋ ተጎጂዎች እና ተጋላጮች ግዴታ</u>

የአደጋ ተጎጂዎች እና ተጋላጮች የሚከተሉት ግዴታዎች ይኖሩባቸዋል፡-

፩/ አደገኛ ከሆነ አንድ ስፍራ እንዲለቁ ወይም ወደ አንድ ሥፍራ እንዳይገቡ ሥልጣን ባለው አካል የሚሰጡ ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን የማክበር እና የመፈፀም፤

፪/ ሥልጣን ያለው አካል ለአደጋ አስቸኳይ ምላሽ ለመስጠት የሰው ኃይል፣ አቅርቦቶችን፣ መጓጓዣዎችን፣ መንገዶችን እና መሠረታዊ መገልገያዎችን ለማንቀሳቀስ የሚወስነውን ውሳኔ የማክበር፤

፫/ በአደጋ ሊጠቁ በሚችሉ አካባቢዎች ወይም በመንግሥት ለደህንነታቸው አደጋ ይደርስባቸዋል ተብለው በተለዩ ሥፍራዎች ላይ የኑሮ መሠረት ከማድረግ መቆጠብ፤

1/ To receive information on disaster risk management published by competent authorities;

2/ To participate in the preparation of plans on disaster risk reduction and management; actively participate in social, economic and skill based job creation programs;

3/ To participate in communication and education programs and to improve their knowledge on disaster prevention and control suitable to their practical conditions;

4/ When affected by a disaster, receive humanitarian assistance to the extent of the capacity of the country for specific period in accordance with the law and until rehabilitated;

5/ To participate in supporting the community in the prevention and control of disaster especially by participating voluntarily and freely in charitable activities;

6/ To the extent of their capacity, to actively participate in activities designed to prevent and control disaster.

## 26. <u>Obligations of Victims and Vulnerable People to Disaster</u>

Victims and vulnerables of disaster shall have the following obligations:

1/ Comply with instructions and commands of competent authority to evacuate from hazardous area or not to enter a certain area;

2/ Respect the decisions of competent authority on the mobilization of manpower, supplies, means, equipment and essentials for the immediate response of a disaster;

3/ Refrain from establishing their livelihood in places which are exposed to disaster risk or designated by government as hazardous to their safety;

፬/ የራሳቸውን እና የቤተሰቦቻቸውን ደህንነት ለመጠበቅ ተነሳሽነትን የመውሰድ፤

፭/ ለሚመለከተው የመንግሥት አካል የአደጋ ሁኔታን ባወቁት መጠን በፍጥነት መረጃ የመስጠት፤

፮/ የግለሰቦች የንብረት መብትን ማክበር፤ ተጨማሪ ቀውስና ጉዳትን ከሚያባብስ ተግባራት መቆጠብ፤

፯/ ተፈናቃዮች በሚኖሩበት መጠለያ ውስጥ ከሚደረግላቸው ሰብዓዊ ድጋፍ ጋር በተገናኘ ሰላምን ከሚያውኩ አመለካከትና ተግባራት መታቀብ፤

፰/ ለጉዳት የዳረገው የአደጋ ክስተት ከተቃለለ በኋላ በተቻለ ፍጥነት ራስንና ቤተሰብን ማገገምና መልሶ በተሻለ ሁኔታ በማቋቋም አይበገሬነትን ለመገንባት ያልተቆጠበ ጥረት ማድረግ፡፡

## ክፍል ስድስት
## ስለ ፈንድ መቋቋም

### ፳፯. መቋቋም

በቅድመ አደጋ፣ በአደጋ እና በድህረ አደጋ ወቅቶች ለሚወሰዱ የአደጋ ስጋት ቅነሳ፣ ምላሽና መልሶ ማቋቋም የሚሆን የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድ (ከዚህ በኋላ ፈንድ እየተባለ የሚጠራ) በዚህ አዋጅ ተቋቁሟል፡፡

### ፳፰. የፈንዱ ዓላማ

ፈንዱ የሚከተሉት ዓላማዎች ይኖሩታል፡-

፩/ ፈጣን፣ አስተማማኝ፣ ተገማችና ተጣጣፊ የአደጋ ስጋት ምላሽ የፈንድ ሥርዓትን ተግባራዊ ለማድረግ፤

፪/ በአገር በቀል አቅም ዜጎች፣ ማህበረሰብ እና ተቋማት እርስ በእርስ በመደጋገፍ የአደጋ ስጋትን የመከላከል፣ የማቅለል፣ የዝግጁነት፣ የምላሽ፣ የማገገምና በተሻለ ሁኔታ መልሶ ማቋቋም ላይ ማህበራዊ ኃላፊነታቸውን እንዲያበረክቱ ለማስቻል፤

፫/ የእለት ደራሽ ሰብዓዊ ድጋፍ፣ ስትራቴጂክ መጠባበቂያ ክምችት፣ የቅጽበታዊ አደጋዎች ምላሽ ማሽነሪዎች፣ የክምችት መጋዘኖች እና ቴክኖሎጅዎችን በተሟላ ሁኔታ ለማሟላት፡፡

4/ Take initiatives to protect the safety of their family and themselves;

5/ Immediately provide information within their knowledge to concerned government body regarding a disaster;

6/ Respect private property rights and refrain from acts worsening additional disturbances and damages;

7/ Refrain from attitudes and actions that disrupt peace in relation to humanitarian assistance provided to displaced persons in shelters;

8/ After the incident that caused the damage is alleviated, exert unreserved efforts to build resilience by recovering and reestablishing oneself and the family in a better condition as soon as possible.

## SECTION SIX
## ESTABLISHMENT OF THE FUND

### 27. Establishment

For disaster risk reduction actions to be taken urgently in pre-disaster, during disaster and after disaster, the Ethiopian Disaster Risk Response Fund (hereinafter referred to as the “Fund") is hereby established by this Proclamation

### 28. Objectives of the Fund

The Fund shall have the following objectives:

1/ To implement a fund system that is prompt, reliable, predictable and flexible disaster response;

2/ Enable citizen, community and institutions to contribute their social responsibilities by supporting each other on disaster risk prevention, mitigation, preparedness, response, rehabilitation and better rehabilitation;

3/ To effectively fulfill relief humanitarian support, strategic reserve stock, machineries of emergency disaster, reserve stores and technologies.

**፳፱. የገቢ ምንጭ**

ፈንዱ ከሚከተሉት የገቢ ምንጮች የሚሰበሰብ ይሆናል፡-

፩/ ከአገር ውስጥ ሀብት ማሰባሰቢያ ሥልት የሚገኝ ገቢ፡-

ሀ) ባንኮችና አነስተኛና ጥቃቅን የፋይናንስ ድርጅቶች ከሚሰጡት የብድር መጠን ላይ የሚታሰብ፤

ለ) የዲጂታል ባንኪንግ አገልግሎት ተጠቃሚዎች ከሚከፍሉት የአገልግሎት ክፍያ ላይ የሚስታብ፤

ሐ) የኢንሹራንስ ኩባንያዎች ለሚሰጡት አገልግሎት ከሚሰበስቡት የፕሪሚየም ክፍያ ላይ የሚከፈል፤

መ) ከማንኛውም የአክስዮን ዲቪደንድ ድርሻ፤

ሠ) ከበረራ ትኬት ሽያጭ ፤

ረ) የቴሌኮሚዩኒኬሽን አገልግሎት የሚሰጡ ድርጅቶች ለድምፅና ዳታ አገልግሎት ከሚያስከፍሉት የአየር ሰዓት ዋጋ ላይ፤

ሰ) ከፓስፖርትና ቪዛ አገልግሎት ክፍያ፤

ሸ) ነዳጅ ሽያጭ አቅራቢ ድርጅት ከሚያገኘው ገቢ ላይ፤

ቀ) ማንኛውም የንግድ ፈቃድ በሚወጣበት እና በሚታደስበት ጊዜ በቁርጥ የሚታሰብ፤

በ) የፌደራል ሰነዶች ማረጋገጫና ምዝገባ አገልግሎት ለሚሰጠው አገልግሎት ከሚከፈለው የአገልግሎት ዋጋ ላይ የሚታሰብ፤

ተ) የፌደራል ጉምሩክ ኮሚሽን በሕገ ወጥ ሲዘዋወር ከሚያዘው ዕቃ እና ገንዘብ በዓይነት ወይም በጨረታ ተሸጦ ከሚገኝ ገቢ ፤

ቸ) የኬሚካል አምራች ድርጅቶች ከሚሰጡት የምርት ሽያጭ አገልግሎት ላይ የሚሰበሰብ፤

ኀ) ትንባሆና የአልኮል ምርቶች ሽያጭ አገልግሎት ከሚገኝ ገቢ ላይ የሚታሰብ፤

**29. Source of Income**

The Fund shall be collected from the following sources:

1/ Income from domestic resource mobilization:

a) From loans provided by banks, small and micro finance institutions;

b) From service charges of digital banking users;

c) From the premium collected by insurance companies for their services;

d) From any dividend share of business organizations:

e) From flight tickets;

f) From voice and data air time fee of telecommunication services providers;

g) From Passport and Visa Services;

h) From the income of petroleum supplying enterprises;

i) Lump sum from the registration and renewal of trade licenses;

j) From payment to the services of the Federal Documents Authentication and Registration Services;

k) The Federal Customs Commission receives proceeds from the sale of goods and money seized during illegal trafficking, either in kind or through auction;

l) From the sales of manufacturers of chemical and chemical products;

m) From the sales and service of tobacco and alcohol producers;

ነ) የባህር ትራንስፖርትና ሎጂስቲክ አገልግሎቶች ሽያጭ ላይ የሚሰበሰብ፡፡

፪/ ከለጋሽ አካላት፣ በጎ አድራጎት ድርጅቶች እና ግለሰቦች፤

፫/ ከፌደራሉ መንግስት፣ ከአዲስ አበባና ከድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮች ከጠቅላላው ዓመታዊ በጀት በድርሻ፣

፬/ ከሌሎች ምንጮች ከሚገኝ ገቢ፤

፭/ በዚህ አንቀጽ ከንዑስ አንቀጽ (፩) እስከ (፬) የተመለከተው እንደተጠበቀ ሆኖ ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣ ደንብ መሠረት ተጨማሪ የገቢ ምንጮች ሊወሰኑ የሚችሉ ሲሆን በእያንዳንዱ ዘርፍም ምን ያህል መጠን መዋጣት እንዳለበትም በዚሁ ደንብ ይወሰናል፡፡

## ፴. የመንግስትና የግል ተቋማት ግዴታዎች

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ የተዘረዘሩትን አገልግሎቶች የሚሰጡ ተቋማት በደንቡ የሚወሰነውን ክፍያ ሰብስበው ለፈንዱ ሂሳብ በወቅቱ ገቢ የማድረግ ግዴታ አለባቸው።

## ፴፩. የፈንዱ አጠቃቀምና አስተዳደር

ፈንዱ፡-

፩/ የአደጋ ስጋት ምላሽ የማስፈፀሚያ የበጀት ክፍተት መኖሩ ሲረጋገጥና ክፍተቱን በአፋጣኝ መሙላት አስፈላጊ ሲሆን፤

፪/ ቅጽበታዊ አደጋ ሲፈጠርና የተከሰተውን አደጋ የአስቸኳይ ምላሽ ቅድሚያ መስጠቱ አስፈላጊነት ሲታመንበት፤

፫/ የዕለት ደራሽ ሰብዓዊ ድጋፍ፤ ስትራቴጂክ መጠባበቂያ ምግብና ምግብ-ነክ ያልሆነ ክምችት እንደየአስፈላጊነቱ ለማምረት ወይም ግዥ ለመፈፀም፤ የክምችት መጋዘኖች አቅምን ለማሳደግና ተያያዥ መሠረተ-ልማት ለማስፋፋት፤

፬/ ፈንዱን ለማሳደግ የሚያስችሉ የገቢ ማስገኛ ተግባራት ላይ ለመጠቀም፤

፭/ በአደጋ ስጋት ገደብ መሠረት የገንዘብ ወይም የዓይነት ድጋፍ ማድረግ፤

n) From the sales and service of shipping lines and logistic services.

2/ Donation from donors, charitable organizations and individuals;

3/ Share allocation from the annual Budgets of the Federal Government, Addis Ababa and Dire dawa City Administrations;

4/ Income from other sources;

5/ Without prejudice to Sub-Article (1) to (4) of this Article, the Council of Ministers may issue a Directive to determine additional sources and the amount of contribution from each source.

## 30. Obligations of Government and Private Institutions

Institutions providing services as listed under Article 29 of this Proclamation shall have the obligation to collect the fees determined by the Regulation and deposit the money to the fund's account within the prescribed period.

## 31. Utilization and Administration of the Fund

The Fund can be used:

1/ When it is confirmed that there is a budget deficit to the disaster response and it is becoming necessary to address the deficit;

2/ When there is an emergency disaster and it is believed that emergency response is necessary for the disaster that occurred;

3/ To produce or procure as necessary relief humanitarian support, strategic food and non-food reserves, and to strengthen the capacity of reserve warehouses and expand related infrastructures;

4/ To use the fund on income generating activities that can grow the fund;

5/ To provide financial or in-kind supports based on the disaster threshold;

፮/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት እንደ አስፈላጊነቱ ፈንዱ የሚተዳደርበትን ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፴፪. የፈንዱ የሒሳብ መዝገብና ኦዲት

፩/ የፈንዱ የሒሳብ መዛግብት እና ገንዘብ ነክ ሰነዶች በየዓመቱ በዋና ኦዲተር ወይም ወይም እርሱ በሚሰይመው ኦዲተር ይመረመራሉ፡፡

፪/ ፈንዱን የሚያስተዳደረው አካል የኦዲት ሪፖርቱን የበጀት ዓመቱ በተጠናቀቀ በአራት ወራት ውስጥ ተጠሪ ለሆነለት አካል ማቅረብ አለበት፡፡

## ፴፫. የበጀት ዓመት

የፈንዱ በጀት ዓመት የመንግስት የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

## ፴፬. የተከለከሉ ተግባራት

የሚከተሉትን ድርጊቶች መፈፀም የተከለከለ ነው፡-

፩/ የሰብዓዊ እርዳታ ሥርጭት አቅጣጫን ማስቀየር፤ እርዳታው ለታለመለት ዓላማ እንዳይውል ማድረግ፣ መሸጥ፣ ፍቃድ ሳይኖር ይዞ መገኘት ወይም ወደ ሶስተኛ ወገን ማስተላለፍ፤

፪/ ማንኛውም በፌደራል ሆነ በክልል ደረጃ የሚገኝ አመራር አካል የቅድመ ማስጠንቀቂያ ሥርዓቱ በሚሰጠው የማስጠንቀቂያ መረጃን ተቀብሎ ተገቢው የጥንቃቄ እርምጃ ሳያደርግ ሆን ብሎ ወይም በቸልተኝነት በሰው ሕይወትና በኑሮ መሠረተ-ልማት ላይ የከፋ ጉዳት እንዲደርስ ማድረግ፤

፫/ የሰብዓዊ እርዳታ ድጋፍ ለማግኘት ሀሰተኛ መረጃ ወይም የተጋነነ ጥያቄን ማቅረብ፤

፬/ ለተጎጂዎች የሰብዓዊ እርዳታ በማንኛውም ሁኔታ በወቅቱ እንዳይደርስ ማዘግየት ወይም እንዳይደርስ ማድረግ፤

፭/ ሰብዓዊ እርዳታ ድጋፍ ለማይገባው ሰው መስጠት፤

6/ The Council of Ministers may issue a Regulation for the administration of the Fund.

## 32. Books of Accounts and Audit

1/ The Fund’s books of accounts and financial documents shall be Audited annually by the Auditor General or an Auditor assigned by it.

2/ The Administrator of the Fund shall submit the audit report to the body to which it is accountable within four months after the end of the budget year.

## 33. Budget Year

The Fund’s budget year shall be government’s budget year.

## SECTION SEVEN
## MISCELLANEOUS PROVISIONS

## 34. Prohibited Acts

Committing the following acts is prohibited:

1/ Diverting the distribution direction of humanitarian aid, preventing the aid from reaching to the targeted purpose, selling, possessing without authorization or transferring to third person;

2/ Causing intentionally or by negligence severe damage to human lives and livelihoods by any administrator found at the federal and regional levels failing to take appropriate precautionary measures despite receiving warning information from the early warning system;

3/ Providing false information or making exaggerated request with the intention of procuring humanitarian aid;

4/ Delaying or preventing humanitarian aid in any form from reaching on time to victims of disaster;

5/ providing humanitarian aid to person not entitled;

፮/ አደጋ ሳይኖር አደጋ እንዳለ አድርጎ የእርዳታ ጥያቄን ማቅረብ፤

፯/ የአደጋ ስጋትን የሚያባብሱ እና አደጋዎቹን የሚፈጥሩ የትኛውም ዓይነት ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፤ ማህበራዊና አካባቢያዊ ድርጊቶች ላይ የመሳተፍ፤

፰/ በተረጅነት እና በጠባቂነት አስተሳሰብ በሰብዓዊ ድጋፍ ማዕቀፍ ለተራዘመ ጊዜ መቆየት፤

፱/ የሰብዓዊ ድጋፍን ከተመደበለት ድርሻ ወይም መጠን በላይ ለመውሰድ መሞከር፤ ወይም መውሰድ፤

፲/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ መሠረት የኢትዮጵያ አደጋ ስጋት ምላሽ ፈንድን በወቅቱ አለመሰብሰብ፤ የተሰበሰበውን ገንዘብ በየወሩ መጨረሻ ወደ ፈንድ አካውንቱ ገቢ አለማድረግ፤ መዘግየት ወይም በሪፖርት አለመግለፅ፤

፲፩/ የሰብዓዊ ድጋፍ የምግብ ነክ ቁሳቁስ መያዣ ስታንዳርዱን ያልጠበቀ መሆን፤ የሚጠበቀውን መረጃ የሌለው ፤ በመያዣው ላይ የተገለፀው ከውስጡ ይዘት ጋር የማይጣጣም መሆን፤ የምግብ እህሉን ከባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ ማቅረብ፡፡

## ፴፭. አስተዳደራዊ ቅጣት እና ወለድ

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፳፱ የተዘረዘሩትን የፈንዱን ገቢዎች በሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚወጣው ደንብ መሠረት ሰብስቦ ለፈንዱ የባንክ ሂሳብ ገቢ ያላደረገ ድርጅት ወይም ተቋም ዋናውን ገንዘብ እና የባንክ ወለድ አስር ከመቶ ቅጣት ጨምሮ እንዲከፍል ይገደዳል፡፡

## ፴፮. የወንጀል ተጠያቂነት

ማንኛውም ሰው፡-

፩/ የሰብዓዊ እርዳታ ለተረጂዎች እንዳይደርስ ያደናቀፈ ወይም የከለከለ እንደሆነ እስከ አስር ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ የሰብዓዊ እርዳታን ለራሱ ወይም እርዳታው ለማይመለከተው ሰው ጥቅም እንዲውል ያደረገ እንደሆነ የተዘረፈውን ንብረት

6/ submitting false relief request while there is no disaster;

7/ Participating in any type of political, economic, social and environmental activities which may aggravate or create disaster risk;

8/ Staying in humanitarian support framework for prolonged period of time weaponizing incompetency and dependency;

9/ Attempting or taking humanitarian aid beyond the allocated share or amount;

10/ Failure to collect on time, deposit to the Fund's account within the prescribed period, delay or failure to submit report regarding the Fund as provided under Article 29 of this Proclamation.

11/ The packaging of humanitarian food supplies does not meet the standards; does not contain the required information; does not match the contents stated on the container; presents the food grains mixed with foreign substances.

## 35. Administrative Penalty and Interest

An organization or institution which fails to deposit the income of the Fund listed under Article 29 of this Proclamation within the prescribed period shall be obliged to pay the principal money with interest as determined by the National Bank of Ethiopia and 10% of the amount not deposited as penalty.

## 36. Criminal Responsibilities

Any person who:

1/ Obstructs or prohibits humanitarian aid from reaching to the beneficiaries shall be punished with rigorous imprisonment up to 10 years.

2/ Diverts humanitarian aid for himself or for another person not entitled to receive shall be punished with rigorous imprisonment

ማስመለሱ ወይም መውረሱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከአስር ዓመት እስከ ሀያ አምስት ዓመት በሚደርስ ጽኑ እስራት እና እስከ ብር ፩ ሚሊዮን (አንድ ሚሊዮን ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፫/ የሰብዓዊ እርዳታ ድጋፍ ለማግኘት ሀሰተኛ መረጃ የሰጠ ወይም የተጋነነ ጥያቄ ያቀረበ ወይም አደጋ ሳይኖር አደጋ እንዳለ አድርጎ የእርዳታ ጥያቄ ያቀረበ እንደሆነ ከስድስት ወር በማያንስ እና ከአንድ ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ያስቀጣል፡፡

፬/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፫) ድንጋጌ ቢኖርም የተሰጠው ሀሰተኛ ማስረጃ በመንግስት ንብረት ወይም በተጠቃሚዎች መብት ላይ ከባድ ጉዳት ያደረሰ በሆነ ጊዜ የደረሰውን ጉዳት ከግምት ውስጥ በማስገባት ከአንድ ዓመት በማያንስ እና ከሦስት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና እስከ ብር ፲፭ ሺህ (አስራ አምስት ሺህ ብር) በሚደርስ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል፡፡

፭/ የሰብዓዊ ድጋፍ የምግብ ቁሳቁስ መያዣ ስታንዳርዱን ያልጠበቀ መሆን፤ የሚጠበቀውን መረጃ የሌለው ፤ በመያዣው ላይ የተገለፀው ከውስጡ ይዘት ጋር የማይጣጣም ፤የምግብ እህሉን ከባዕድ ነገሮች ጋር ቀላቅሎ ያቀረበ መሆኑ በማስረጃ ሲረጋገጥ አግባብ ባለው ሕግ ይቀጣል፡፡

## ፴፯. <u>የመተባበር ግዴታ</u>

ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ ለኮሚሽኑ እና ለተጠሪ ተቋማቱ የተሰጣቸውን ሥልጣን እና ተግባራት ለመወጣት በሚያደርጉት እንቅስቃሴ የመተባበር ግዴታ አለበት፡፡

## ፴፰. <u>የተሻሩ እና ተፈፃሚነት የማይኖራቸው ሕጎች</u>

፩/ የአስፈፃሚ አካላት ሥልጣንና ተግባር መወሰኛ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፷፫/፪ሺ፲፬ አንቀጽ ፸ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፪/ የመጠባበቂያ ምግብ ክምችት ኤጀንሲ ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፪፻፹፬/፪ሺ፭ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

from ten years to twenty five years and fine up to 1,000,000 Birr (One Million Birr) in addition to the confiscation or returning of the looted aid items.

3/ Whoever provides false information or makes an exaggerated claim in order to obtain humanitarian assistance, or makes a claim for assistance under the pretext of a danger when there is no danger, shall be punished by simple imprisonment for not less than six months and not more than one year.

4/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (3) of this Article, where the false evidence provided causes serious damage to government property or the rights of users, it shall be punishable by simple imprisonment for a term not less than one year and not more than three years and a fine not exceeding Birr 15,000 (Fifteen Thousand Birr), taking into account the damage caused.

5/ If the humanitarian aid food packaging does not meet the standards; does not have the required information; does not match the contents stated on the packaging; or is proven to have mixed the food with foreign substances, shall be punishable with the appropriate law.

## 37. <u>Duty to Cooperate</u>

Every person shall have the duty to cooperate with the Commission and the institutions made accountable to it in carrying out their powers and duties under this Proclamation.

## 38. <u>Repealed and Inapplicable Laws</u>

1/ Article 70 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs Proclamation No. 1263/2021 is hereby repealed by this Proclamation.

2/ Strategic Food Reserve Agency Establishment Council of Ministers Regulation No. 284/2013 is hereby repealed by this Proclamation.

፫/ የብሔራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር ፫፻፷፫/፪ሺ፰ በዚህ አዋጅ ተሽሯል፡፡

፬/ በዚህ አዋጅ ከተደነገጉ ጉዳዮች ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ እና ልማዳዊ አሰራር በዚህ አዋጅ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

## ፴፱. ደንብና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን

፩/ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ ደንቦችን ያወጣል፡፡

፪/ ኮሚሽኑ በዚህ አዋጅ እና ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጡ ደንቦች ላይ የተሰጡትን ተግባራት እና ኃላፊነት ለማስፈፀም የሚያስፈልጉ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል፡፡

## ፵. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፳፩ ቀን ፪ሺ፲፯ ዓ.ም**

**ታዬ አጽቀሥላሴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

3/ National Disaster Risk Management Commission Establishment Council of Ministers Regulation No. 363/2015 is hereby repealed by this Proclamation.

4/ Any law and customary practice contrary to this Proclamation shall have no effect on matters covered by this Proclamation.

## 39. Power to Issue Regulations and Directives

1/ The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the execution of this Proclamation

2/ The Commission may issue Directives necessary to carry out its duties and responsibilities provided by this Proclamation and Regulations to be issued for the execution of this Proclamation.

## 40. Effective Date

This Proclamation shall enter into force as of the day of its publication on the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Abeba, on this 28th Day of July, 2025.**

**TAYE ATSKESELASSIE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**